# የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት በኢትዮጵያ

አስቻለው አሻግሬ*

## አህጽሮተ-ጽሑፍ

በማንኛውም ዘመናዊ የታክስ ሥርዓት ውስጥ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል ልዩ ልዩ አለመግባባቶች እንደሚከሰቱ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የታክስ ሥርዓት እነዚህ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸው ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፎችን መዘርጋትና ሥራቸውን በትክክል እንዲሠሩ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በእኛ ሀገርም ዘመናዊ የታክስ ሕጎች ከታወጁበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚስተናገዱባቸው የሕግና የተቋማት ማዕቀፎች ተዘርግተዋል፡፡ የዚህ አጭር ጽሑፍ ዋና ዓላማ አሁን በኢትጵያ ተግባራዊ የተደረጉት የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓቶች የታክስ ከፋዩን ቅሬታዎች አስተማማኝና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በማስተናገድ፣ የታክስ ከፋዩን የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት መብት በተሟላ መልኩ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር ነው፡፡ ይህ ጸሐፊ በዚህ የምርምር ሥራ እንደተገነዘበው በኢትዮጵያ ውስጥ የተዘረጉት የታክስ ከፋዮች ቅሬታ የሚፈቱባቸው ሥርዓቶች ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ጥቅም ያደሉ በመሆናቸው የታክስ ከፋዩን ቅሬታዎች ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በማስተናገድ የታክስ ከፋዩን ፍትሕ የማግኘት መብት በአስተማማኝ ሁኔታ የሚያረጋግጡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ፀሐፊ አመለካከት የታክስ ከፋዩን የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት የማይገሰስ መብት ትርጉም ባለው ሁኔታ ለማረጋግጥ ሚዛናዊ የሆነ የታክስ ቅሬታ አፈታት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ስለሆነ አሁን ያለውን የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት እንደገና መፈተሽና ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## ቁልፍ ቃላት

ታክስ፣ ግብር፣ ታክስ ከፋይ፣ የታክስ ከፋይ ቅሬታ፣ የታክስ ከፋይ ቅሬታ አፈታት፣ አጣሪ ኮሚቴ፣ የግብር ይግባኝ ጉባኤ፣ ይግባኝ፣ የሕግ ስህተት፣ የማስረዳት ሸክም፡፡

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v8i1.6

---

* ኤል.ኤል.ቢ፣ኤል.ኤል.ኤም፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሕግና አስተዳደር ጥናቶች ኮሌጅ፣ በሕግ ት/ቤት የሕግ መምህር (ሌክቸረር)፣በማናቸውም ፍርድ ቤት ጠበቃና የሕግ አማካሪ፡፡
የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ቃለመጠየቅ ላደረገላቸውና እጅግ ጠቃሚ ሓሳቦችን ለሰጡት ለአቶ ጌታቸው ታደሰ፣ ለአቶ ዳዊት ተሾመና ለዶ/ር ታደሰ ሌንጮ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ይህ ጸሐፊ የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ በማንበብ በጣም ጠቃሚና ገንቢ አስተያየቶችን የሰጡትን ስማቸው ያልተገለጸ የውስጥና የውጭ ገምጋሚዎች (anonymous internal and external assessors) ከልብ ያመሰግናቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳች ስህተት ቢገኝበት ኃላፊነቱ የጸሐፊው ብቻ ነው፡፡ በጽሑፉ ላይ አስተያየት ወይም ትችት ቢቀርብበት ጸሐፊው ደስተኛ እንደሚሆን እየገለጸ፣ ለማንኛውም ግንኙነት የጸሐፊው የኢ-ሜይል አድራሻ gakidan.ashagre335@gmail.com ነው፡፡

# Tax Appeal Procedures in Ethiopia: Summary

No matter how good a tax system might be, disputes between the Tax Authority and the taxpayers are unavoidable, and this necessitates putting in place legal and institutional frameworks that regulate such disputes and give adequate remedies to aggrieved taxpayers. Since the 1940s, Ethiopia's tax laws embodied provisions on tax appeal procedures with a view to providing for the right of taxpayers to be heard. The same is true with the current tax laws of the country. The current tax appeal procedures include the *Review Committee* under the auspices of the Tax Authority. However, the accountability of this organ to the Tax Authority renders its neutrality and impartiality questionable. Moreover, the powers accorded to this organ are confined to tax assessment issues. Another challenge encountered by a taxpayer in the course of using this forum is the requirement to lodge complaints against a contested tax assessment within ten days from the reception of notice of assessment. This seems to be very short.

The second institution which receives complaints from taxpayers is the *Tax Appeal Commission* which is, at the federal level, accountable to the Ministry of Justice. However, lodging an appeal to this institution involves two requirements, namely, depositing or paying half of the disputed amount stated in the tax assessment notification, and filing the appeal within thirty days from the decision of the Review Committee or the date of reception of tax assessment made by the tax authority. It can be difficult for taxpayers to deposit half of the disputed amount in cash particularly when the tax assessment is made with bad intentions, such as unmet corruption expectations, on the part of a tax assessor.

Even if aggrieved taxpayers are able to take their cases to the Tax Appeal Commission, it may not guarantee fair and impartial treatment for the following reasons. First, although the Tax Appeal Commission seems to have an independent structure, it is directly accountable to the Ministry of Justice which may affect its independence and impartiality as its members are selected and appointed by the Minister. Secondly, some members of the Commission come from the Ethiopian Revenue and Customs Authority and Ministry of Finance and Economic Development which are sources of (or affiliated to) the tax assessments against which the appeal is lodged. In effect, these two organs of the government become judges on their own cases thereby adversely affecting the right of aggrieved taxpayers to an impartial decision.

In Ethiopia, taxpayers aggrieved by the decision of the Tax Appeal Tribunal can take their case to the competent appellate court on questions of law only. The gaps and ambiguities in the distinction between *questions of law* and *questions of fact*, however, necessitate guidelines that can positively contribute toward restricting the discretionary power of regular courts in rejecting appeals by misinterpreting questions of law as questions of fact.

## መግቢያ

መንግሥት የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ገቢ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው። የማንኛውም መንግሥት ገቢ ምንጭ ደግሞ ታክስና[1] ታክስ-ነክ ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ናቸው። የየትኛውም ሀገር መንግሥት ከፍተኛው ገቢውን የሚያገኘው ታክስ በመጣልና በመሰብሰብ ነው። ስለሆነም ማንኛውም መንግሥት ታክስ የመጣል እና የመሰብሰብ ሥልጣን አለው። መንግሥት ይህንን መብት የሚያገኘው ከታክስ ከፋዮች ጋር በሚያደርገው ስምምነት ሳይሆን መንግሥት በመሆኑ ብቻ ነው። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ለመንግሥት ታክስ ለመክፈል የሚገደደው ለሚከፍለው ታክስ ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ከመንግሥት ወዲያውኑ ወይም ዘግይቶም ቢሆን ስለሚያገኝ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም ታክስ መክፈል የማይገዳደሩት ግደታ ስለሆነ ነው።[2] ይሁን እንጂ ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ሰፊውን የማኅበረሰብ ክፍል የሚነካ ሕጋዊ ግዴታ እንደመሆኑ መጠን የታክስ ሥርዓቱ መልካም የታክስ ሥርዓቶች መግለጫ ባህሪያትን ሊያካትት ግድ ይለዋል።[3] ሆኖም ግን አንድ የታክስ ሥርዓት የቱንም ያህል መልካም የታክስ ሥርዓት መገለጫዎችን በማካተት የተዋቀረ ቢሆን፣ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ታክሱን በሚያስተዳድርበት ወቅት በታክስ ከፋዮች ላይ የተለያዩ ቅሬታዎችን መፍጠሩ የማይቀር ነው።[4] እንኳንስ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የተሟላና ዘመናዊ የታክስ ሥርዓት ባልተዘረጋባቸው ሀገራት ቀርቶ የታክስ ሥርዓታቸው እጅግ ዘመናዊ ሆኗል በሚባሉት ሀገሮችም እንኳ የታክስ ከፋዮች ቅሬታ የሚስተዋል ክስተት ነው።

---

[1] በእኛ ሀገር ‘ግብር’ የሚለው ቃል እጅግ የተለመደ ቢሆንም ግብርንና ታክስን በተለዋዋጭነት መጠቀምም የተለመደ አነጋገር ሆኗል። እንደሚታወቀው ታክስ የሚለው ቃል የእንግሊዝኛ ቃል ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በሀገራችንም ውስጥ ልክ እንደማንኛውም የአማርኛ ቃል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ልብ ማለት የሚያስፈልገው ግን ታክስ የሚለው ቃል ማንኛውንም ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ የሚያካትት ሲሆን፤ ግብር የሚለው ቃል ግን እንደ ገቢ ግብር ያሉትን ቀጥተኛ የታክስ ዓይነቶች ብቻ የሚሸፍን መሆኑን ነው። ለምሳሌ ያህል *ብላክስ ሎው* በመባል የሚታወቀው የሕግ መዝገበ-ቃላት ታክስ የሚለውን ቃል “a monetary charge imposed by government on persons, entities, transactions or property to yield public revenue…..most broadly, the term embraces all governmental impositions on persons, property, privileges, occupations, and enjoyments of the people and includes duties, imposts and excises,” በማለት ይተረጉመዋል፤ Bryan A. Garner(ed.), *Black’s Law Dictionary*, 8th ed., 2004, ገጽ 1496 ላይ ይመልከቱ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት *ግብር* የሚለውን ቃል *ገቢ ያለው ዜጋ ሁሉ በተወሰነ ጊዜ እንደገቢው መጠን ለመንግሥት የሚከፍለው የተወሰነ ገንዘብ ነው* በማለት ይፈታዋል። *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ በ2001 ዓ.ም ተሻሽሎ የታተመ፣ ገጽ 499 ይመልከቱ። በመሆኑም ይህ ጸሐፊ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚጠቀመው ታክስ የሚለውን ቃል ሲሆን፣ ግብር የሚለውን ቃል የተጠቀመው አስፈላጊ በሆነበት ሥፍራ ብቻ ነው። ታክስና ግብር የሚሉት ቃላት በተለዋዋጭነት የማያገለግሉ በመሆኑ፣ ግብር የሚለው ቃል በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለቦታው ገብቶ ቢገኝ ታክስ የሚለውንም ቃል ወክሎ የገባ እንደሆነ አንባቢዎች እንዲገነዘቡለት ጸሀፊው ከወዲሁ በአክብሮት ያሳስባል።

[2] HL Bhatia, *Public Finance,* 24th ed., 2005, ገጽ 37።

[3] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 43።

[4] ዋና ዋና የሚባሉት የታክስ ከፋይ ቅሬታዎች ከተቀናሽ፣ ከወለድ፣ ከቅጣት፣ ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ ከሽያጭ መሣሪያ አጠቃቀም፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ክፍያዎች፣ ከጉምሩክ ቀረጥና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቅሬታዎች ናቸው።

በመሆኑም ማንኛውም የታክስ ሥርዓት የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡[5] ምክንያቱም በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶች በእነዚህ ሁለት አካላት መካከል ያለውንና ወደፊትም የሚኖረውን ግንኙነት ማበላሸታቸው አይቀርም፡፡ የእነዚህ ሁለት አካላት ግንኙነት መበላሸት ደግሞ በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን የመደጋገፍ፣ አብሮ የመሥራት ስሜትና ለአንድ ሀገራዊ ግብ የመሰለፍ ዝንባሌ በጣም ይጐዳዋል፡፡[6] እንዲህ ያለው ሁኔታ በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማምጣቱም አይቀርም፡፡[7] በመሆኑም በእነዚህ ሁለት አካላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ወይም ግጭቶች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በሠለጠነ መንገድ መፈታት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ዓላማ እውን ለማድረግ የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋል አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም የዓለማችን ሀገሮች የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱባቸውን ልዩ ልዩ ዘዴዎች ቀይሰው ሥራ ላይ አውለዋል፡፡[8] የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚፈቱባቸው (የሚስተናገዱባቸው) ሥርዓቶች ከሀገር ሀገር የተለያዩ ስያሜዎችና አደረጃጀቶች ቢኖሯቸውም በአጠቃላይ ግን እነዚህ ቅሬታዎች በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች (administrative tribunals)፣ በመደበኛ ፍ/ቤቶች ወይም በአማራጭ አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች[9] (alternative dispute resolution methods) የሚፈቱ ናቸው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘመናዊ የታክስ ሕጎች በማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ የጀመረችው ከ1933 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱባቸው የሕግና የተቋማት ማዕቀፎችና አሠራሮች ሥራ ላይ እንደዋሉ የሀገሪቱን የታክስ ሕግ ታሪክ በመመርመር የምንገነዘበው ነው፡፡[10] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ ኢትዮጵያ ከወሰደቻቸው ዋና ዋና ርምጃዎች

---

[5] የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓት ካልተዘረጋ የታክስ ከፋዮችን የመሰማት መብት ለማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም፡፡

[6] Misganaw Gashaw, 'The Room for Alternative Dispute Resolution (ADR) Process in Tax Disputes: A Message to the Ethiopian Tax Administrations,' in Yazachew Belew (ed.), The Resolution of Commercial/Business Disputes in Ethiopia: Towards Alternatives to Adjudication? *Ethiopian Business Law Series*, Vol.5, ገጽ 25፡፡

[7] ዝኒ ከማሁ፡፡

[8] ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የሚከተለውን የምርምር ሥራ ይመልከቱ፣ Victor Thuronyi, How Can an Excessive Volume of Tax Disputes Be Dealt With? December 2013, available at <www.imf.org/external/np/leg/tlaw/2013/eng/tdisputes.pdf>, accessed on September 30, 2014.

[9] Misganaw Gashaw፣ ከላይ በማስታወሻ ቀጥር 6 የተጠቀሰ፣ ገጽ 28፡፡ አቶ ምስጋናው ጋሻው በግልጽ እንዳቀረበው አማራጭ የአለመግባባት ዘዴዎች የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎችን ለመፍታት በሀገረ እንግሊዝ፣ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በቻይና፣በህንድ በብራዚል፣ በኔዘርላንድስ፣ በፓኪስታን፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በግሪክ እና በመሳሰሉት ሀገሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡እንደዚሁም ደግሞ የሚከተለውን የምርምር ጽሁፍ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡- Melinda Jone and Andrew J Maples (2012), 'Mediation as an Alternative Option in Australia's Tax Disputes Resolution Procedures', *Australian Tax Forum*, 27 ፣ available at <www.delta search.com/?q=melinda+jone+and+Andrew+J+Maples%2c+Mediation+AS+Alternative +Dispute+option+in Australia's Tax Dispute+R, pdf>, accessed on June 26,2013..

[10] ስለሀራችንን የታክስ ሕጎች፡- Taddese Lencho, "Towards Legislative History of Modern Taxes in Ethiopia (1941-2008)," *Journal of Ethiopian Law*, 25, No.2, 2012, ከገጽ 104-158 ያለውን ይመልከቱ፡፡

አንዱ የታክስ ሥርዓቱን ማሻሻል ነው፡፡[11] የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራሙ መሠረታዊ የሆኑ ግቦችን ታሳቢ በማድረግ የተጀመረ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ መሠረታዊ ግቦችም ለመንግሥት ገቢ ማስገኘት፣ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን ማረጋገጥ፣ ፍትሐዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል ማረጋገጥና የታክስ ሥርዓቱን ማዘመን ናቸው፡፡[12] በዚህም መሠረት እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ የተጀመረው የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ እርምጃ የተጠናቀቀው ዘመናዊነት የሚታይባቸው የተለያዩ የታክስ ሕጎችን በማውጣት ነው፡፡ ከእነዚህም ሕጎች ዋና ዋናዎቹ የገቢ ግብር ሕግ (እንደተሻሻለ)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ (እንደተሻሻለ)፣ የተርን ኦቨር ታክስ ሕግ (እንደተሻሻለ)፣ የቴምብር ቀረጥ ሕግ (እንደተሻሻለ)፣ የጉምሩክ ቀረጥ ሕግ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ሕግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡[13] እነዚህን አዋጆች ስንመረምራቸው ታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱባቸውን ሥርዓቶች የዘረጉ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ በእነዚህ ሕጎች ውስጥ ታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚያቀርቡባቸውን፣ የሚስተናገዱባቸውንና እልባት የሚያገኙባቸውን ሥርዓቶች መፈተሽና መተንተን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ ጽሑፍ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ታክስ ከፋዮች በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ውሳኔ ቅር በተሰኙ ጊዜ ቅሬታቸውን ለአጣሪ ኮሚቴ፣ ለታክስ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አልያም ደግሞ ለመደበኛው ፍ/ቤት (በይግባኝና በሰበር ደረጃ) ለማቅረብና ለማሰማት ፍትሐዊነት የሚታይበት አካሄድ የተዘረጋላቸው መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም በማድረግ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ መፍትሔ የሚያሻቸውን ዋና ዋና የሕግና የአተገባበር ችግሮችን ለመጠቆም ሙከራ አድርጓል፡፡ የዚህን ጽሑፍ ዓላማ እውን ለማድረግና ተጨባጭ ጠቀሜታ የሚኖረው ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት መሠታዊ የሕግ ምርምር ዘዴዎች (legal research methods) ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎችም አግባብነት ያላቸውን ጽሁፎች መዳሰስ (literature review)፣ ሕግንና ውሳኔዎችን የመተንተን ዘዴ (legal and case analysis)፣ ቃለ-መጠይቆችና ተያያዥ የምርምር ዘዴዎች ናቸው፡፡

የዚህ ጽሑፍ መነሻና መድረሻ (scope of the research work) የተወሰነው የተመረጠውን ርእስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ርዕስ ተገቢውን ሽፋን ለመስጠት በፌደራል መንግሥት ሥራ ላይ የዋሉት ዋና ዋና የታክስ ሕጎች ተዳስሰዋል፡፡ ሆኖም ግን የታክስ ይግባኝ ጉዳይን በተመለከተ በሕጎቹ መካከል ከፍተኛ መመሳሰል ስለሚስተዋል በጽሑፉ ውስጥ አላስፈላጊ ድግግሞሽ እንዳይኖር ለማድረግ የማጣቀስ ዘዴ (cross-reference) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን የጽሑፉ ርዕስ በአጠቃላይ ስለኢትዮጵያ የታክስ ቅሬታ አፈታት ሥርዓት የሚናገር ቢሆንም ጸሀፊው የምርምር ሥራውን በሠራበት ጊዜ የክልሎችን አሠራር ለመፈተሽ ሙከራ አላደረገም፡፡ ይሁን እንጂ የክልል የታክስ ሕጎች ከፌደራል መንግሥት የታክስ ሕጎች ጋር እጅግ ተመሳሳይ በመሆናቸው ይግባኝን አስመልክቶ በፌደራል መንግሥት የታክስ ሕጎች ላይ የሚደረግ ትንተና የክልሎቹንም ሕጎች ለመረዳት ያስችላል፡፡

---

[11] Alemayehu Geda, Readings on the Ethiopian Economy, 2011, Addis Ababa University Press, ከገጽ188-204::

[12] Taddese Lencho, '*Articulating Ethiopia's Current Tax Polciy: Sources and Fundamental Objectives*,' in Taddese Lencho and Kyle Logue (eds.), Ethiopian Tax System: Some Contemporaray Issues and Problems, Ethiopian Business Law Series, Vol.VI, 2014, ከገጽ 1-26 ያለውን ይመልከቱ፡፡

[13] እነዚህን አዋጆች ወደፊት ስለምንጠቅሳቸው እዚህ ላይ ሙሉ ስማቸውንና የወጡበትንም ዓመተ-ምህረት መጥቀስ አላስፈለገም፡፡

ይህ ጽሑፍ በሚከተለው አኳኋን ተዋቅሯል፡፡ በጽሑፉ የመጀመሪያ ክፍል የታክስ አስገቢውን ባለሥልጣን ሥልጣናትና ኃላፊነቶች፣ የታክስ ከፋዮች ዋና ዋና መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች መነሻ ምክንያቶች በአጭሩ ተዳሰዋል፡፡ በሁለተኛው ክፍል የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት ታሪካዊ ዳራ ከተገለፀ በኋላ፣ በሦስተኛው የጽሑፉ ክፍል ታክስ ከፋዮች ለግብር አጣሪ ኮሚቴ፣ ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ እና ለመደበኛው ፍርድ ቤት ቅሬታቸውን በማቅረብ መፍትሔ የሚያገኙባቸው ሥነ-ሥርዓቶችና አሠራሮች ተፈትሸዋል፡፡ በመጨረሻም በምርምር ጽሑፉ የተገኙት ችግሮችና ማጠቃለያ ሓሳቦች ቀርበዋል፡፡

# 1. ስለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን እና ስለታክስ ከፋዮች ጥቂት ነጥቦች

## 1.1 የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሥልጣናትና ኃላፊነቶች

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከፍተኛውን የመንግሥት ገቢ ድርሻ የሚይዘው ከታክስ የሚገኘው ገቢ እንደመሆኑ፣ መንግሥት ይህንን ገቢ አስተማማኝ በሆነ መልኩ ለማግኘት ታክስን በሕግ መሠረት ለመሰብሰብና ለማስተዳደር ብቃት ያለው የመንግሥት ተቋም (የታክስ አስገቢ ባለሥልጣን) ማቋቋም ያስፈልገዋል፡፡ በሀገራችን ዘመናዊ የታክስ ሥርዓት ሥር መስደድ የጀመረው የጣሊያን ወረራ ከተቀለበሰበት ከ1933 ዓ.ም ወዲህ ስለሆነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሥራውን ሲያከናውን እንደቆየ የሀገሪቱ የታክስ ሥርዓት ታሪክ ያስገነዝበናል፡፡[14]

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል ደረጃ ታክስን የሚያስተዳድሩ የመንግሥት መ/ቤቶች ተቋቁመው ታክስ የማስተዳደሩን ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀደም ሲል በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የነበሩት ተቋማት የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ[15]፣ የፌደራል መንግሥት ገቢዎች ቦርድ፣[16] የገቢዎች ሚኒስቴር[17] እና የጉምሩክ ባለሥልጣን[18] ቢሆኑም ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ገቢዎችና

[14] Melkamu Belachew (2003), *Powers and Functions of the Federal Inland Revenue Authority and the Position of the Tax Appeal Commission,* Senior Thesis, unpublished,Faculty of Law, Addis Ababa University ,ገጽ 32:: ቀደም ሲል የነበረው የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የተለያዩ ስያሜዎች እንደነበሩት በየጊዜው የታወጁት ሕጎች ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ስያሜዎች የገቢ ግብር መምሪያ፣ የአገር ውስጥ ገቢ አስተዳደር፣ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እና የመሳሰሉት ነበሩ፡፡

[15] የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 61/1989፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣3ኛ ዓመት፣ቁጥር 1፣ እንደዚሁም ደግሞ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 367/95 ይመልከቱ፡፡

[16] የፌዴራል መንግሥት ገቢዎች ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 5/1987፣ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፡፡

[17] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ( እንደተሻሻለ)፣ አዋጅ ቁጥር 471/1998፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 12ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ አንቀጽ 9(8) እና አንቀጽ 20ን ይመልከቱ፡፡

[18] የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋሚያና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 60/1989፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18ን ይመልከቱ፡፡

ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ተቋቁሟል፡፡[19] ይህ መ/ቤት የተቋቋመው የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባላሥልጣን፣ የጉምሩክ ባለስልጣንና የገቢዎች ሚኒስቴር በአንድ ላይ ተዋህደው ነው፡፡[20] ይህም የተደረገበት ምክንያት እነዚህ ሦስቱ ተቋማት በተመሳሳይ ዓላማ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸውና ተመሳሳይ የሀብት አጠቃቀምና የአደረጃጀት ስልት የሚከተሉ በመሆናቸው የሦስቱ ተቋማት መዋሃድ ዘመናዊ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት፣ የሀብት አጠቃቀምንና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡[21] እንደዚሁም ደግሞ ከጥር 1 ቀን 2003 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ የአዲስ አበባ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ እና የፌደራል መንግሥት ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥራቸውን በአንድ ማእከል በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡[22]

አሁን በፌደራል ደረጃ በሥራ ላይ ያለው የታክስ ባለሥልጣን በማቋቋሚያ አዋጁ የተመለከቱት የላቁ ዓላማዎች ግባቸውን ይመቱ ዘንድ ተገቢውን ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም ይረዳው ዘንድ ማቋቋሚያ አዋጁ ዘርዘር ያሉ ሥልጣናትን የሰጠው ሲሆን ቁልፍ የሆኑ ኃላፊነቶችም አብረው እንደተጣሉበት አዋጁ ያስገነዝባል፡፡ እነዚህም የባለሥልጣኑ ሥልጣናትና ተግባራት በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 6 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቀደም ሲል ለገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለጉምሩክ ባለሥልጣንና ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣናትና ኃላፊነቶች ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እንደተላለፉ ማቋቋሚያ አዋጁ ያስገነዝበናል፡፡ በዚህም መሠረት ቀደም ሲል የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ባለሥልጣንና የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ይሠሩባቸው የነበሩትን ሥልጣናት የአሁኑ መ/ቤት ይሠራባቸዋል፤ ይህ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት የቀድሞዎቹን ተቋማት ኃላፊነቶች መወጣት ግዴታ አለበት ማለት ነው፡፡[23] የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሥልጣናት ሕግ የማውጣት የውክልና ሥልጣን ያለው ስለሆነ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን በማውጣት ሥራ ላይ ያውላል፡፡[24]

### 1.2 የታክስ ከፋዮች ዋና ዋና መብቶችና ግዴታዎች

መንግሥት ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣኑን ሊሠራበት የሚገባው የሕግ የበላይነትንና የታክስ ከፋዮችን ዋና ዋና መብቶች ያለማወላወል በማክበር ነው፡፡[25] ለምሳሌ

[19] የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 587/2000፣ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣14ኛ ዓመት፣ ቁጥር 44፡፡

[20] ዝኒ ከማሁ፣ የዚህን አዋጅ መግቢያ ይመልከቱ፡፡

[21] ዝኒ ከማሁ፡፡

[22] በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የመጡ ሠራተኞች ድልደላ መመሪያ፣ መመሪያ ቁጥር 48/2003፣ ያልታተመ፡፡

[23] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 22ን ይመልከቱ፡፡

[24] ምክንያቱም አሁን በሀገራችን ባለው የፖለቲካ ሥርዓት አጠቃላይ የታክስ መርሆች የተቀመጡት በ1987 ዓ.ም ተግባራዊ በተደረገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ሲሆን ዝርዝር ጉዳዮችን የያዙ የታክስ አዋጆች በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣አዋጆቹን ለማስፈፀም የሚጠቅሙ ደንቦች ደግሞ በሚኒስትሮች ም/ቤት ወጥተው በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የገቢ ግብር ድንብ፣ ደንብ ቁጥር 78/1994፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 37 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ፣ ደንብ ቁጥር 79/1994፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19 ተጠቃሾች ናቸው፡፡

[25] Satish C. Wadhawan and Clive Gray, Enhancing Transparency in Tax Administration: A Survey of African Economic Policy, Discussion Paper Number 3 July 1998, available at <www.Frp.2.org/…/Tax%20Administration/Enhncing%20Transparancey%,pdf\>, accessed on June 29 2013.

ያህል የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩን በትህትናና በአክብሮት መያዝና መቀበል ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ታክስ ከፋዩ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ያገኘ የራሱ መብትና ክብር ያለው ሲሆን፣ ይህም መብት መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ነው፡፡[26] ከዚህም በተጨማሪ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ከፋዮችን በሕግ ፊት እኩል ሆኖ የመታየት መብታቸውን ማክበር ይኖርበታል፡፡[27] በመሆኑም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን የጉዳዩ ፍሬ ነገር በሚመራው መሠረት ሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል እንጂ አድልኦ ማድረግ አይገባውም፡፡ ይህንንም የታክስ ከፋዩን መብት እውን ለማድረግ እያንዳንዱ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ ለዘመዶቹ ወይም ለወዳጆቹ ልዩ ጥቅም መስጠት የለበትም፤ በሌላው ታክስ ከፋይ ላይም ያልተገባ በደልና አድልኦ መፈጸም አይኖርበትም፡፡[28]

በሦስተኛ ደረጃ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የግል ሕይወት ምስጢራዊነት ጥበቃ መብት ያለው[29] በመሆኑ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ታክስ ሲጥልና ሲሰበስብ ከታክስ ከፋዩ የሚያገኘውን መረጃ ለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ከመግለጽ መቆጠብ አለበት፡፡[30] በአራተኛ ደረጃ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ሀብት የማፍራትና በሀብቱም የመጠቀም ሕገ-መንግሥታዊ መብት ያለው በመሆኑ[31] ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በታክስ ከፋዩ ላይ የሕገ-መንግሥትና የሌሎች ተዋረድ ሕጎች መሠረት የሌለው ታክስ በመጣልና በመሰብሰብ የታክስ ከፋዩን በንብረቱ የመጠቀም መብት አላግባብ ሊያጣብበት አይገባም፡፡ እንዲሁም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ታክስ የመሰብሰብ ተግባሩን ሲወጣ በታክስ ከፋዩ ላይ ቅሬታ መፍጠሩ የማይቀር ስለሆነ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይም ለቅሬታው ተገቢውን መፍትሔ ለማግኘት የሚያስችሉት አስተማማኝ የሕግና ተቋማዊ ማዕቀፍ ሊዘረጉለት ይገባል፡፡[32]

በሌላ በኩል ግን ማንኛውም መብት ተነፃፃሪ ግዴታ ያለበት ስለሆነ በታክስ ከፋዩም ላይ ሕግ የሚጥላቸው ልዩ ልዩ ግዴታዎች አሉ፡፡ የታክስ ከፋዩ ግዴታዎች ዓይነትና መጠን ከሀገር ሀገር የተለያዩ ቢሆኑም በታክስ ከፋዩ ላይ ግዴታ የማይጥል የታክስ ሥርዓት ይኖራል ብሎ ማሰብ ግን ፈጽሞ አይቻልም፡፡ አሁን በሀገራችን ውስጥ በሚሠራባቸው የታክስ ሕጐች መሠረት ዋና ዋና የሚባሉት የታክስ ከፋዮች ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግደታ

በሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ግደታ ያለበት ማንኛውም ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ እንዳለበት በዘመናዊ የታክስ አስተዳደርና ሥርዓት ውስጥ ሁነኛ ቦታ የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ታክስ ከፋዮች የታክስ ከፋይ መለያ

---

26 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣አንቀጽ 18ን ይመልከቱ፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ሀገራችን አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችም ይህንን መብት በግልጽ ደንግገዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ1948 ዓ.ም የወጣውን የተባበሩት መንግሥታት ሁሉን ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት መግለጫ እና እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም የወጣውን ዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶችን ስምምነት ይመልከቱ፡፡

27 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 25፡፡

28 የገቢ ግብር አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 286/1994 (እንደተሻሻለ) ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 34፣ አንቀጽ 40(1)፡፡

29 የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 26፡፡

30 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 39፡፡

31 የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 40፡፡

32 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 37፡፡

ቁጥር እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1993 ዓ.ም አውጥታለች፡፡[33] ይህም ሕግ በ1953 ዓ.ም የወጣውን የገቢ ግብር ሕግ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ሲሆን በዚህ የማሻሻያ አዋጅ ሥር በግልጽ እንደተደነገገው ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡[34] ይኸው ግዴታ በ1994 ዓ.ም በወጣው የገቢ ግብር አዋጅም ምንም ዓይነት መሠረታዊ ለውጥ ሳይደረግበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡[35]

### ለ) ግብርን የመያዝና የመክፈል ግዴታ (Duty to withhold and pay)

ይህ ግዴታ በታክስ ከፋዮች ላይ የተጣለ ወሳኝ ግዴታ በመሆኑ በዘመናዊ የታክስ ሥርዓት ወስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ግደታ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥም በታክስ ከፋዮች ላይ ከተጣሉት ግደታዎች አንደኛው መሆኑን የሀራችንን የታክስ ሕጎች በመዳሰስ እንገነዘባለን፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ[36] አንቀጽ 10 ሥር በግልጽ እንደተመለከተው ማንኛውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው የወር ደመወዝ ላይ ከተቀጣሪው የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ በማስቀረት የተቀነሰውን ግብር ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በየወሩ ገቢ የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡[37] ከዚህም በተጨማሪ በገቢ ግብር አዋጅ[38] አንቀጽ 53 በግልጽ እንደተደነገገው በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ገንዘብ ከፋዮች ከተከፋይ ሒሳቦች ላይ 2% ቀንሰው ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡[39] ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪም የፈጠራ መብትን በመከራየት ለአከራዩ ክፍያ የሚፈጽም ከፋይ 5% የገቢ ግብር ቀንሶ በመያዝ የተቀነሰውን በገቢ ግብር በሕጉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን፣[40] የአክሲዮን ድርሻ ለባለአክሲዮኖች የሚያከፋፍል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወይም አክሲዮን ማኅበር ከክፍያው ላይ 10% የገቢ ግብር ቀንሶ በማስቀረት በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡[41]

### ሐ) የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ

ይህ ግዴታ የታክስ ከፋዮች መሠረታዊ ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም ታክስ ከፋዮች ይህንን ግዴታቸውን በትክክል የሚወጡ ከሆነ የታክስ ከፋዮችን ጠቅላላ ገቢ፣ ተቀናሽ የሚደረጉ ወጭዎችን፣ ግብይቶች የተደረጉባቸውን ክፍያዎች፣ ክፍያዎች የተፈፀሙባቸውን ጊዜ እና

---

[33] ከማናቸውም ገቢ ግብር ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ( ማሻሻያ)፣አዋጅ ቁጥር 227/1993፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣

[34] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2(1) ይመልከቱ፡፡

[35] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 43፡፡

[36] የገቢ ግብር አዋጅ ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰው ነው፡፡

[37] እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ሁሉም ቀጣሪዎች ግብር ከፋዮች አለመሆናቸውን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሠራተኛ የትምህርት ሚኒስቴር ተቀጣሪ ቢሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠራተኛውን የገቢ ግብር ቀንሶ ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የማስተላለፍ ግዴታ ቢኖርበትም ግብር ከፋይ ግን አይደለም፡፡ በሌላ መልኩ የኢትዮጵያን ንግድ ባንክ ብንወስድ ይህ ቀጣሪ ራሱ በገቢ ግብር አዋጅ በሠንጠረዥ "ሐ" ሥር የቢዝነስ ታክስ ከፋይ ሲሆን በሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት ከሠራተኞች ላይ የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረትና ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የማስተላለፍ ሕጋዊ ግዴታ አለበት፡፡

[38] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፡፡

[39] ዝርዝር ሁኔታውን በሚገባ ለመገንዘብ የገቢ ግብር ደንብ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 24 እና 25ን ይመልከቱ፡፡

[40] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 35(1)፡፡

[41] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 34(1)፡፡

*የታክስ ከፋዮችን ትርፍ ወይም ኪሣራ ለማወቅ ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ በ1952 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. 1960) በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት ማንኛውም በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ወይም ድርጅት የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡*[42] *ወደ ታክስ ሕጎቻችን ስንመጣም በ1994 ዓ.ም የታወጀው የገቢ ግብር አዋጅ ሥር ከሚታወቁት ሦስት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ውስጥ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የሚከራዩ ሕንጻዎች ባለቤት የሆኑ የደረጃ "ሀ" እና የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሒሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ እንዳለባቸው ይኸው ሕግ ደንግጓል፡፡*[43] *ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የደረጃ ሐ ታክስ ከፋዮች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግደታ የሌለባቸው መሆኑን ነው፡፡*

**መ) ገቢን የማሳወቅና ታክስ የመክፈል ግዴታ**

*በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕግና በሌሎች የታክስ ሕጐች በታክስ ከፋዮች ላይ ከተጣሉት ግዴታዎች ውስጥ ዋነኛዎቹ ገቢን ማሳወቅና ታክስን መክፈል ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ማንኛውም በገቢ ግብር አዋጅ የሚሸፈን ግብር ከፋይ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ገቢውን ማሳወቅና ታክሱን መክፈል ይኖርበታል፡፡*[44] *እንደዚሁም ደግሞ በተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ*[45]*፣ በተርን ኦቨር ታክስ ሕግና*[46] *በኤክሳይዝ ታክስ ሕግ*[47] *ውስጥ እንዲህ ያለው ግዴታ*

---

[42] *የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት መንግሥት የንግድ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 166/1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣19ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣ ከአንቀጽ 63-70 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመልከቱ፡፡ ሆኖም ግን ይኸው ሕግ አነስተኛ ነጋዴዎች የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ እንደማይኖርባቸው በልዩ ሕግ ሊደነገግ እንደሚችል በግልጽ አስቀምጧል፡፡*

[43] *የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(16) መሠረት ሦስት የግብር ከፋዮች ደረጃዎች ቢኖሩም የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች ግን የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግደታ እንደሌለባቸው የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 48 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው መሠረታዊ ጥያቄ ለመሆኑ በገቢ ግብር አዋጁ ውስጥ ታሳቢ የተደረጉትን ሦስት የግብር ከፋይ ደረጃዎች አንዱን ከአንዱ ለይተን የምናውቀው እንዴት ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ግልጽና የማያሻማ መልስ የሚሰጠን ደግሞ የገቢ ግብሩን ለማሟላት ተብሎ የወጣው የገቢ ግብር ደንብ ነው (ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰ)፡፡ በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 መሠረት የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የሚባለው በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወይም የአንድ ዓመት ጠቅላላ ገቢው አምስት መቶ ሺህ ብር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሌላ የንግድ ሥራ የሚሠራ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ማንኛውም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዓመት ውስጥ የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ወይም የካፒታሉ መጠን ምንም ይሁን ምን በደረጃ "ሀ" ሥር የሚወድቅ መሆኑን ነው፡፡ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ደግሞ በደረጃ "ሀ" ሥር ሊወድቅ የሚችለው የካፒታሉ መጠን ወይም የሚያገኘው ዓመታዊ የትርፍ መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው አምስት መቶ ሺህና ከዚያ በላይ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ግብር ከፋይ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ነው የሚባለው የዓመት ጠቅላላ ገቢው ከ100,000.00 ብር በላይ እስከ 500,000.00 ብር የሚደርስ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው እስከ መቶ ሺህ የሚደረስ ግብር ከፋይ (ግለሰብ መሆን አለበት) ደግሞ የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ እንደሆነ ደንቡ ያስገነዝበናል፡፡*

[44] *የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰው፣ ከአንቀጽ 64-76 ያሉትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም የገቢ ግብር ደንቡ ውስጥ ከአንቀጽ 18-25 ያሉትን ሀተታዎች ይመልከቱ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰ፡፡*

[45] *የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 285/1994፣ (እንደተሻሻለ)፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 33፣አንቀጽ 26፡፡*

[46] *የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣(እንደተሻሻለ)፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣9ኛ ዓመት፣ ቁጥር 21፣አንቀጽ 10፡፡*

በታክስ ከፋዮቹ ላይ ተጥሎባቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ታክስ ከፋዮች ገቢያቸውን የሚያሳውቁትና የሚፈለግባቸውን ታክስ የሚከፍሉት በተመሳሳይ ጊዜ ሳይሆን እያንዳንዱ የታክስ ሕግ ለይቶ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### ሠ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብና ደረሰኝ የመቁረጥ ግዴታ

በኢትዮጵያ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተግባራዊ የሆነው ከጥር 1995 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ በዚህ ሕግ[48] መሠረት ማንኛውም ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርብና በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት በተጨማሪ እሴት ታክስ ሕጉ የተመለከተውን አስገዳጅ የምዝገባ መስፈርት አሟልቶ የተገኘ እንደሆነ ወይም ወደፊት አሟላለሁ የሚል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖረው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡[49] በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22 እንደተደነገገው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሂድ ሰው ዕቃዎቹን ወይም አገልግሎቶቹን ለሚያቀርብለት ሰው ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡[50]

### ረ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ

ይህ የታክስ ክፋይ ግዴታ በሌሎቹ ሀገሮች ቆየት ያለ[51] ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን ይህ ግዴታ በታክስ ከፋዮች ላይ የተጣለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሚኒስትሮች ም/ቤት በነሐሴ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት ነው፡፡[52] ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት ዝርዝራቸው የተወሰነ ታክስ ከፋዮች በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ዕውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመጠቀም የሽያጭ ደረሰኞችን አዘጋጅተው የማውጣት ግዴታ አለባቸው፡፡[53]

---

47 የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣አዋጅ ቁጥር 307/1995 (እንደተሻሻለ)፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣9ኛ ዓመት፣ ቁጥር 20፣አንቀጽ 6-7፡፡

48 የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 45 የተጠቀሰ፡፡

49 ዝኒ ከማሁ፣ ይህንንም ሓሳብ አስመልክቶ አዋጁ በአንቀጽ 16 ሥር ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ የሚኖርበት በማናቸውም የአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከ500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ ከሆነ ወይም በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከ500,000.00 ብር በላይ ይሆናል ብሎ መገመት የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት የኖረ እንደሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ እንደሚኖርበት በግልጽ ደንግጓል፡፡

50 ዝኒ ከማሁ፣ ሆኖም ግን ሕግ በሚፈቅዳቸው ልዩ ሁኔታዎች ታክስ የሚከፈልበት እቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ ሰዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለመቁረጥ የማይገደዱባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ የአዋጁ አንቀጽ 22(6)(7) የደነገጉትን ይመልከቱ፡፡

51 ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳካ ሥራ የሚሠራ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የፈጠረው በአሜሪካን ሀገር የኦሀዮ ግዛት ይኖር የነበረው ጀምስ ሪቲ (James Ritty) ሲሆን ለዚህ የፈጠራ ሥራውም እ.ኤ.አ በ1879 ዓ.ም የፈጠራ ሥራ ባለቤትነት (ፓተንት) ተሰጥቶታል፡፡ "Cash Register." Microsoft® Encarta® 2009 [DVD]. Redmond, WA: Microsoft Corporation, 2008ን ይመልከቱ፡፡

52 በሽያጭ መሳሪያዎች ስለመጠቀም ግደታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፣ ደንብ ቁጥር 139/1999፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣13ኛ ዓመት፣ ቁጥር 48፡፡

53 በዚህ ረገድ ዝርዝር ጉዳዮችን ለመገንዘብ ሁሉንም የደንቡን ድንጋጌዎች ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ደንቡን ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንም ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ መመሪያ በማውጣት እየሰራበት ይገኛል፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግደታ የተጣለባቸው የደረጃ ሀ እና የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች ናቸው፡፡

### 1.3 በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች መነሻ ምክንያቶች፡ አጭር ዳሰሳ

ይህ የመንግሥት መ/ቤት በሕግ የተጣሉበትን አያሌ ተግባራት ሲያከናውንና ልዩ ልዩ ኃላፊነቶቹን ሲወጣ ከታክስ ከፋዮቹ ጋር መጋጨቱ የሚጠበቅና የማይቀር ነው፡፡[54] በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል ለሚነሱ አለመግበባቶች ምክንያቶቹ በጣም በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋና የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡ *አንደኛ* አንድ የታክስ ሕግ የተፈጻሚነት ወሰን በግልጽ አለመታወቅ የአለመግባባት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን በማስፋት ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ብርቱ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን ታክስ ከፋዩ ደግሞ የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን አጥብቦ በመተርጐም ከታክስ ኃላፊነት ለማምለጥ ሙከራ ያደርጋል፡፡[55] እንዲህ ያለው ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዩ መካከል አለመግባባት ይፈጠራል፡፡[56]

በ*ሁለተኛ* ደረጃ የአንዳንድ የሕግ ድንጋጌዎች ግልጽ አለመሆን አለመግባባትን ሊያስከትል እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ *ሦስተኛ* የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ወይም ታክስ ከፋዩ የታክስ ሕግ ድንጋጌዎች የሚያስተላልፉትን ትክክለኛ መልዕክት አለመረዳት አለመግባባትን ሊያስከትል ይችላል፡፡[57] *አራተኛ* ታክስ ከፋዩ የታክስ ሕጐቹ የሚጥሉበትን ግዴታዎች በአግባቡ ሳይወጣ ሲቀር አለመግባባት ይከሰታል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በላይ እንደጠቀስነው ማንኛውም የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት ብለናል፡፡ እነዚህ የሂሳብ መዝገቦች ሲያዙም ተቀባይነት ያለውን የሂሳብ አያያዝ መርህ በመከተል የሚዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡[58] ሆኖም ታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ሳይዝ ሲቀር፣ አልያም ደግሞ የሂሳብ መዝገቡ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ዘንድ ተቀባይነት ሲያጣ፣ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ከእንደዚህ ዓይነቱ ታክስ ከፋይ ላይ ታክሱን የሚሰበስበው በግምት ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡[59] በግምት ላይ ተመሥርቶ

---

[54] P.P. Graig (2003), *Administrative Law*, Sweet and Maxwell, ከገጽ 93-121 ይመልከቱ፡፡

[55] B.B. Lal and N.Vashisht (2006), *Direct Taxes: Income Tax,Wealth and Tax Planning*,26th ed., Pearson Education, ከገጽ 43-54 ያለውን ይመልከቱ፡፡

[56] *ዝኒ ከማሁ፣ ለምሳሌ ያህል ይህ ጸሐፊ በሙያ ሥራው አጋጣሚ የተረዳው አንድ ጉዳይ እዚህ ላይ ቢነሳ የተያዘውን ጭብጥ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ስሙን እዚህ ላይ ለመግለጽ ያልተፈለገ አንድ ድርጅት ዋና የንግድ ሥራው ሠራተኞችን ወደ ዐረብ ሀገራት መላክ ነበር፡፡ ይህ ድርጅት እነዚህን ሰዎች ወደ ዐረብ ሀገራት በመላክ ዐረብ ሀገራት ከሚገኙት አገናኝ ኤጀንሲዎች ገቢ የሚያገኝ በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈለግበትን የገቢ ግብር ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በየጊዜው ሲከፍል የነበረ ቢሆንም በአንድ ወቅት ግን የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ይህ ድርጅት የተርንኦቨር ታክስ መክፈል እንደሚኖርበት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ይልክለታል፡፡ ደርጅቱ ግን የሰው ኃይል አቅርቦቱ ተግባር ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጠ አገልግሎት ስለሆነ እኔን የሚመለከተኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ እንጂ የሀገር ውስጥ ግብይቶችን ለመግዛት የታወጀው የተርንኦቨር ታክስ ሕግ ሊሆን አይገባውም በማለት ተቃውሞውን አቀረበ፡፡ በዚህም ምክንያት በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዩ መካከል አለመግባባት ሊፈጠር ችሏል፡፡*

[57] *ዝኒ ከማሁ፡፡*

[58] የሒሳብ መዝገብ የሚያዘው ተቀባይነት ያለውን የሒሳብ መዝግብ አያያዝ ደንብ ተከትሎ እንደሆነ የገቢ ግብር ሕጋችን የደነገገ መሆኑን ለመረዳት የገቢ ግብር አዋጁን ( ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣) አንቀጽ 17ን ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም ደግሞ የሚከተለውን ጥናታዊ ጽሁፍ ይመልከቱ፡- Belay Eshetu, *Assessment of Income Tax Under the Ethiopian Income Tax Law: Examination of Current Practice,* Senior Thesis,unpublished, Faculty of Law, Addis Ababa University, 1998፣ ከጽ 17-25 ያለውን ይመልከቱ፡፡

[59] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 67፡፡

የሚወሰነው የታክስ መጠን ደግሞ በታክስ ከፋዩ ዘንድ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ በሁለቱ መካከል አለመግባባት ይፈጠራል፡፡ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዩ መካከል ክርክር ሊፈጥር የሚችለው *አምስተኛ* ምክንያት አንድ ፍሬነገር ተከስቷል ወይም አልተከሰተም የሚል አለመግባባት ነው፡፡ ለአብነት ያህል አንድ ታክስ ከፋይ በአንድ የታክስ ዘመን ኪሳራ ገጥሞኛል ሲል የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ደግሞ ታክስ ከፋዩ ትርፍ አግኝቷል ሊል ይችላል፡፡

## 2. የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት በኢትዮጵያ፡ ታሪካዊ ዳራ (1933 ዓ.ም. እስከ 1987 ዓ.ም)

ኢትዮጵያ እጅግ ጥንታዊ ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ እንደመሆኗ መጠን[60] የታክስ ጉዳይም ጥንታዊነት ያለው ክስተት እንደሆነ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡[61] ሆኖም ዘመናዊ የታክስ ሕጐች መውጣት የጀመሩትና ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት የጀመረው የኢጣሊያ ወረራ በ1933 ዓ.ም ከተቀለበሰ በኋላ መሆኑ[62] ቀደም ሲል ተገልጧል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚፈቱባቸው ሥርዓቶች በሕግ ተደንግገው ሲሠራባቸው እንደነበር በተለያዩ ጊዜያት ወጥተው የነበሩት የታክስ ሕጐች ያሳያሉ፡፡ ይህንን ጥቅል አባባል አፍታትቶ ለማቅረብ አግባብነት ያላቸውን የታክስ ሕጎች እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩ እንዳስሳቸዋለን፡፡[63]

በመጀመሪያ ደረጃ በ1936 ዓ.ም ወጥቶ በነበረው የገቢ ግብር አዋጅ የገንዘብ ሚኒስቴር በወሰነበት የግብር ልክ ተጎዳሁ የሚል ግብር ከፋይ የግብር ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኙን እንደሚያቀርብ ተደንግጎ ነበር፡፡[64] ከዚህም በመቀጠል በ1941 ዓ.ም ወጥቶ የነበረውም የገቢ ግብር አዋጅ የታክስ ከፋይ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት ዘርግቶ እንደነበር አዋጁን በማንበብ እንገነዘባለን፡፡[65] ከዚህ አዋጅ በመቀጠል የወጣው የ1949 ዓ.ም የገቢ ግብር ድንጋጌ[66] ሲሆን በዚህ የገቢ ግብር ድንጋጌ አንቀጽ 50 መሠረት ንጉሠ-ነገሥቱ በአዲስ አበባና በወቅቱ በነበረው አጠራር በሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶችና ካስፈለገም በእያንዳንዱ አውራጃ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮኖች ሊሾም እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ የእነዚህ የይግባኝ ከሚሲዮኖች አሿሿምም ለሕዝቡ የሚገለፀው በመንግሥት ማስታወቂያ (በነጋሪት ጋዜጣ) እንደሚሆን

[60] Margarey Perham (1968), *The Government of Ethiopia*, London፡ Faber & Faber Limited, ገጽ 10.

[61] Richard Punkhrust (1968), *The Economic History of Ethiopia,1800-1935,* Haileselassie University Press,Addis Ababa, Ethiopia, 504-544::

[62] Taddese Lencho፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 10 የተጠቀሰ ፣ ገጽ 105፡፡

[63] *ያለፈውን ማወቅ የአሁኑን ለመገንዘብና የወደፊቱን ለመተንበይ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዶ/ር ታደሰ ሌንጮ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 10 በተጠቀሰው የምርምር ሥራቸው አንድ እውቅ የአሜሪካን ሀገር ደራሲ አባባል ጠቅሰው እንዳቀረቡት "ያለፈው ጊዜ ሙት አይደለም፤ እንዲያውም ያለፈው ጊዜ ያለፈም አይደለም፡"* (ትርጉም የራሴ)

[64] ስለሰዎችና ሥራዎች ሁሉ ግብር እንዲከፈል የሚወስን አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 60/1936፣ነጋሪት ጋዜጣ፣3ኛ ዓመት፣ቁጥር 9፣ አንቀጽ 5(i-vii)::

[65] ከሰዎችና ከሥራዎች ሁሉ ግብር እንዲከፈል የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 107/1941፣ነጋሪት ጋዜጣ፣8ኛ ዓመት፣ቁጥር 12፣ አንቀጽ 5(i-vii)::

[66] ከማናቸውም ዓይነት ገቢ ግብር ስለማስከፍል የወጣ ድንጋጌ፣ ድንጋጌ ቁጥር 19/1949፣ነጋሪት ጋዜጣ፣16ኛ ዓመት፣ቁጥር 1፣ አንቀጽ 5(i-vii)::

ይኸው ድንጋጌ ይገልጻል፡፡[67] በአዲስ አበባና በሸዋ ጠቅላይ ግዛት የሚቋቋመው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን በጠቅላይ ሚኒስቴር ውስጥ የሚተዳደር አንድ ፕሬዝዳንትና ም/ፕሬዝዳንት ያሉበት ሲሆን፣ አባላቱም ከመንግሥት ሠራተኞችና ከነጋዴዎችም የተውጣጡ ሆነው ከአምስት የማያንሱ ከሰባት የማይበልጡ መሆን ነበረባቸው፡፡[68] በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች የሚቋቋመው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን በጠቅላይ ገዥው ሰብሳቢነት ከመንግሥት ሠራተኞች ሦስት ሰዎች እና ከነጋዴዎች ሦስት ሰዎች ያሉበት ነበር፡፡ በአውራጃ ደረጃ የሚቋቋም የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮንም ተመሳሳይ አባላት ሊኖሩት እንደሚችል በዚሁ ሕግ ውስጥ ተደንግጓል፡፡[69]

በዚህም መሠረት በአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን በተወሰነው የግብር ውሳኔ ተበደልኩ የሚል ማናቸውም ግብር ከፋይ ቅሬታውን በመግለጽ ለተገቢው የግብር ይግባኝ ከሚሲዮን በጽሑፍ ሊያመለክት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡[70] ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለውም የግብሩ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ነው፡፡[71] ይግባኙ በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ ግን በሀገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የተወሰነው ግብር ትክክለኛና የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ በዚያው መሠረት እንደሚፈፀም በግልጽ ተደንግጓል፡፡[72] ይህ ድንጋጌ የግብር ይግባኝ የሚታይበትን የሥልጣን እርከን ጨምሮ ይዟል፡፡ በመሆኑም ግብር ከፋዩ ቅር የተሰኘው በገንዘብ ሚኒስቴር የሀገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ከሆነ ይግባኙን የሚያቀርበው በአዲስ አበባ ለነበረው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ሲሆን ይግባኙ በማናቸውም ጠቅላይ ግዛት የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን ውሳኔ ላይ ከሆነ በዚያው ጠቅላይ ግዛት ለተሾመው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ወይም ለአውራጃው በተለይ ለተሾመ ኮሚሲዮን የሚቀርብ ነበር፡፡[73]

በማናቸውም ደረጃ የሚገኘው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ይግባኝ የተባለበትን የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ውሳኔ ለማጽናት፣ ለመቀነስ፣ ለመጨመር ወይም ለመሰረዝ እንዲሁም ደግሞ ለጉዳዩ ፍጻሜ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ተጨማሪ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር፡፡[74] ይሁን እንጂ ማንኛውም የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ወይም ግብር ከፋዩ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ከፈጠረበት የውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ባሉት ሠላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለከፍተኛው ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጎ ነበር፡፡[75] ከፍተኛው ፍ/ቤትም በዚህ *ነገር የተነሳውን ክርክር ተመልክቶ የሚሰጠው ከሕግ የተቃወሰውን ብቻ አቃንቶ ወደ ኮሚሲዮኑ ይመልሳል እንጂ በግምቱ ሥራ አይገባም።*[76] (አንክሮ የተጨመረ)፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘው ወገን (የግብር አስገቢው ባለሥልጣን

[67] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 51፡፡
[68] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 50(ሀ)፡፡
[69] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 50(ሐ)፡፡
[70] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 54፡፡
[71] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55፡፡
[72] ዝኒ ከማሁ፡፡
[73] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 56፡፡
[74] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 57፡፡
[75] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 59፡፡
[76] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 60፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔውን መስጠት ይችል የነበረው በሕግ ጉዳዮች ብቻ እንጂ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ለመመርመርና ውሳኔ ለማስተላለፍ ያልተፈቀደለት መሆኑን ነው፡፡

ወይም ግብር ከፋዩ) ቅሬታውን ለንጉሠ-ነገሥቱ ጠቅላይ ፍ/ቤት የማቅረብ መብት ነበረው፡፡[77]

ስለግብር ይግባኝ በምናወሳበት ወቅት በኢትዮጵያ ዘመናዊ የታክስ ሕጎች ታሪክ ውስጥ ጉልቶ የሚታየው በ1953 ዓ.ም ወጥቶ የነበረውና የተለያዩ ማሻሻያዎች እየተደረጉበት እስከ 1994 ዓ.ም ሥራ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ነው፡፡[78] ይህ አዋጅ መጀመሪያ ሲወጣ በጠቅላላው 74 አንቀጾች የነበሩት ሲሆን ከአንቀጽ 49 እስከ 61 የነበሩት አንቀጾች የግብር ይግባኝ ሥርዓትን የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 49 እንደተገለፀው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮኖቹ የሚሾሙት በንጉሠ-ነገሥቱ ነበር፡፡[79] የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 50 እንደሚደነግገው እያንዳንዱ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን አንድ ሊቀመንበር፣ አንድ ምክትል ሊቀመንበርና እንዲሁም ቢያንስ አምስት አባሎች የሚገኙበት ሲሆን የአባሎቹ ስብጥርም ግማሾቹ ከነጋዴዎችና ከፕሮፌሽናሎች ወይም የቮኬሽናል ሥራ ከሚሠሩ ሰዎች መካከል መመረጥ ነበረባቸው፡፡

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 54(ሀ) መሠረት በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የግብር ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ግብር ከፋይ አግባብነት ላለው የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ይግባኙን ማቅረብ ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ግን ግብር ከፋዩ ይግባኙን ማቅረብ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ንዑሳን አንቀጾች የተመለከቱትን ጥብቅ ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልቶ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ በአንቀጽ 54(ለ) ሥር እንደተመለከተው ሥራዎችንና ፕሮፌሽናል፣ ወይም ቮኬሽናል ሥራ የሚሠራ ሰው ወይም ማኅበር ይግባኝ ለማቅረብ በአንቀጽ 55 የተወሰነው ሠላሳ ቀን ከማለፉ በፊት ለይግባኝ መክፈቻ ይሆን ዘንድ ቢያንስ በሀገር ውስጥ መ/ቤት ከተወሰነው ግብር ላይ 75% ወይም በይግባኝ ባዩ ላይ ባለፈው የግብር ዘመን የመጨረሻው ግብር ታስቦ ከተወሰነው ልክ ላይ በመቶ ሰባ አምስት (75%) ዝቅተኛ የሆነው ተመርጦ በመያዣነት መክፈል አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የመያዣ ገንዘብ ግብር ከፋዩ በአዋጁ አንቀጽ 46(ሀ) መሠረት ባስታወቀው ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ግብር በማናቸውም ምክንያት ማነስ አይኖርበትም፡፡[80] በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54(መ) እንደተመለከተው ግብር ከፋዩ ግብር እንዲከፍል የተጠየቀው ለመጀመሪያ ጊዜ በሚሆንበት ጊዜ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 54(ለ) የተመለከተው ቅድመ-ሁኔታ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ ይልቁንም እንዲህ ዓይነቱ ግብር ከፋይ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ቢያንስ ባስታወቀው ገቢው ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ሃምሳ በመቶ (50%) ወይም የገቢ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ በግብር አስገቢው መ/ቤት እንዲከፍል ከተጠየቀው ግብር ላይ ግማሹን (50%) ይግባኙን ለማቅረብ በተወሰነው የ30 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ መክፈል ይኖርበታል፡፡[81]

[77] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 61፡፡

[78] ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 173/1953፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣20ኛ ዓመት፣ቁጥር 13፡፡

[79] ዝኒ ከማሁ፣በገንዘብ ሚኒስቴር ሥር የነበረው የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት የሚወሰነውን ግብር የሚመለከት አንድ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮንና ኮሚሲዮኖቹ ተሹመው በሚገኙበት ሥፍራ የነበሩ የአውራጃ፣ ወይም የወረዳ የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤቶች ስለሚወሰኑት ግብር የሚቀርበውን ይግባኝ የሚሰሙ የአውራጃ ወይም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለአንዳንድ ወረዳ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮኖች እንደሚሾሙ ተደንግጓል፡፡

[80] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 54(ሐ)፡፡

[81] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 54(ሠ)፡፡ በአጠቃላይ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 54 በማንበብ እንደምንገነዘበው የዚህ አንቀጽ ንዑሳን አንቀጾች ተፈጻሚነታቸው በሥራዎች (በንግድ ሥራዎች)፣ ፕሮፌሽናል ወይም ቮኬሽናል ሥራ በሚሠሩ ሰዎች (ግብር ከፋዮች) ላይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ግብር ከፋዮች ውጭ ያሉት ግብር ከፋዮች የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር

ለግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የሚቀርብ ማናቸውም ይግባኝ በጽሁፍ ሆኖ የይግባኝ ማመልከቻው ግልባጭ ለአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት ወዲያውኑ ይላክለታል፡፡ ነገር ግን ማናቸውም ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚው ኮሚሲዮን መቅረብ የሚኖርበት የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ነው፡፡ ግብር ከፋዩ በዚህ በተባለው ቀን ውስጥ ይግባኝ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም ደግሞ ማስያዝ የሚገባውን ገንዘብ ሳያስይዝ ወይም ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ በአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት ባለሥልጣን የተወሰነው ግብር ትክክለኛና የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ በዚያው መሠረት በፍጥነት እንደሚፈፀም ተደንግጓል፡፡[82] በሌላ በኩል የአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘና ቅድመ-ሁኔታዎቹን ያሟላ ግብር ከፋይ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ሲያቀርብ አምስት አባላት ያሉበት የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ጉዳዩን ከመረመረና የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ የአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት ባለሥልጣን የሰጠውን የግብር ውሳኔ ለማጽናት፣ ለመቀነስ፣ ለመጨመር ወይም ለመሰረዝ እንዲሁም ደግሞ ለጉዳዩ ፍጻሜ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ ትዕዛዝ ለመስጠት እንደሚችል ነው የተደነገገው፡፡[83] የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ያልሰረዘው እንደሆነ ውሳኔው በፍጥነት ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባው ሕጉ ይገልፃል፡፡[84]

ይሁን እንጂ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤትም ሆነ ግብር ከፋዩ የግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን የሰጠው ውሳኔ "በአንዳንድ ምክንያት በሕግ ... ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ እንደሆነ የተባለው ውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ 30 ቀን ድረስ ጉዳዩን መብቱ ለሚፈቅድለት [ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት] አቅርቦ ስለሕጉ አፈጻፀም [ስለሕጉ አተረጓጐም] ሊጠይቅ ይችላል፡፡"[85] ከዚህ ድንጋጌ በመነሳት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን የሚኖረው በሕግ ጉዳዮች ብቻ ነው ወይስ የፍሬ ነገሮች ክርክሮችንም ይጨምራል ለሚለው ጥያቄ ግልፅ ምላሽ ለማግኘት የሚያዳግት ቢመስልም በአንቀጽ 59 ግን *"መብቱ የሚፈቅድለት ፍ/ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር ተመልክቶ ከሕግ የተቃወሰውን [የሕግ ስህተት ያለበትን] ብቻ አቃንቶ ከፈረደ በኋላ"* ወደ ኮሚሲዮኑ እንደሚመልሰው ደንግጓል፡፡ የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ውሳኔ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ወይም የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወደሚቀጥለው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ተገልጿል፡፡[86] ይግባኙ መቅረብ የሚኖርበትም ይግባኝ የሚለው ወገን የመጀመሪያውን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ውሳኔ ከተቀበለበት ቀን አንስቶ ባሉት ሠላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡[87] ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሊያይ የሚችለው የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚያየውን ጉዳይ ብቻ ነበር፡፡[88] ይህም ማለት

---

የተሰኙ እንደሆነ የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በአንቀጽ 46(*ሀ*) *መሠረት* አስቀድመው ባስታወቁት ገቢ ላይ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ግብር ወይም ገቢያቸውን ያላስታወቁ እንደሆነ እንዲከፍሉ ከተጠየቁት ግብር ግማሹን (50%) ለአገር ውስጥ ገቢ *መሥሪያ* ቤት ገቢ በማድረግ ይግባኛቸውን ለግብር ይግባኝ ሰሚው ኮሚሲዮን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

[82] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55፡፡

[83] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 56፡፡

[84] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 57፡፡

[85] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 58፡፡

[86] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 60፡፡

[87] ዝኒ ከማሁ፡፡

[88] ዝኒ ከማሁ፡፡

የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚያየው የሕግ ጉዳዮችን ብቻ እንደመሆኑ መጠን ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ማየት የሚችለው የሕግ ጉዳዮችን ብቻ ነው ማለት ነው፡፡[89]

ከዚህ በላይ ከመረመርናቸው ሕጐች በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት የወጡ የታክስ ሕጐች ስለይግባኝ የደነገጉትን በመፈተሽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ1955 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው የትራንዛክሽን ሕግ[90] በአንቀጽ 33 በግልጽ እንደተመለከተው፣ በአገር ውስጥ ለሚሠሩ ዕቃዎች ወይም በማናቸውም ስለሽያጭ ገቢ ወይም ስለሕንፃ ሥራ በሚደረገው ታክስ ውሳኔ የማይስማማ ታክስ ከፋይ፣ የሥራ ግብር ይግባኝ ለማየት ሥልጣን ለተሰጠው የግብር ይግባኝ ኮሚሽን የይግባኝ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ይግባኙን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችል የነበረው ሕጉ ያስቀመጣቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነበር፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይግባኙ መቅረብ የሚኖርበት የታክሱ ውሳኔ በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ለግብር ከፋዩ በተሰጠው በ60 ቀናት ውስጥ ነበር፡፡ ሁለተኛ የግብር ከፋዩ ይግባኝ በግብር ይግባኝ ከሚሲዮኑ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ይግባኝ የሚባልበት 60 ቀን ከማለፉ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ ከወሰነው ታክስ 25% የከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡[91] ከዚያም በመቀጠል የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የሚሰኘው ወገን ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊል እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅር ቅሬታ ያደረበት ወገን ደግሞ ወደሚቀጥለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር አልነበረም፡፡ ሆኖም ሁለቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች አከራክረው ሊወስኑ የሚችሉት በሕግ ጉዳይ ብቻ እንጂ ወደ ፍሬ ነገር ጉዳዮች ለመግባት የሚያስችል ሥልጣን አልነበራቸውም፡፡[92]

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት በመስከረም 1967 ዓ.ም ከሥልጣን ሲወርድ በትረ-ሥልጣኑን የጨበጠው የደርግ መንግሥት በርካታ ሥር-ነቀል ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እርምጃዎችን የወሰደ ቢሆንም የታክስ ሕጎችን በተመለከተ ግን ቀድሞ የነበሩትን ሕጎች እያሻሻለ መቀጠልን ነበር የመረጠው፡፡ ሆኖም ግን የደርግ መንግሥት በሀገሪቱ የታክስ ሕጎች ላይ ያደረጋቸው ማሻሻዎች በታክስ ይግባኝ ሥርዓቱ ላይ ትርጉም ያለው ማሻሻዎችን እንዳላደረገ በዚህያን ወቅት የወጡትን ጥቂት ማሻሻዎች በመመረመር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን የደርግ መንግሥት ምንም ዓይነት የታክስ ሕጎች አላወጣም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል በ1968 ዓ.ም የወጣው የገጠር መሬት መጠቀሚያና

---

[89] ጉዳዮችን ወደ መደበኛው ፍ/ቤት መውሰድን በተመለከተ በ1953 ዓ.ም ተግባራዊ የተደረገው የገቢ ግብር አዋጅ በ1949 ዓ.ም ከወጣው የገቢ ግብር ድንጋጌ የተለየ አቋም የያዘ ነበር፡፡ ምክንያቱም በ1949 ዓ.ም በወጣው የገቢ ግብር ድንጋጌ መሠረት የመጀመሪያው የግብር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከፍተኛው ፍ/ቤት ሲሆን ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ነበር፡፡ በኋለኛው ሕግ መሠረት ግን የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደጉዳዩ ሁኔታ የሚወሰን ነበር፡፡ ይህንም ልዩነት በሚገባ ለመገንዘብ የ1949ኙን ድንጋጌ አንቀጽ 59 እና የ1953ቱን አዋጅ አንቀጽ 60 ይመልከቱ፡፡

[90] የትራንዛክሽን ታክስ አዋጅ ቁጥር 205/1955፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣22ኛ ዓመት፣ቁጥር 18፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በ1960 ዓ.ም የወጣው የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 255/1960፣ነጋሪት ጋዜጣ፣ 27ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፣ አንቀጽ 2(የ እና ደ)) በ1953 ዓ.ም በወጣው የገቢ ግብር አዋጅ ላይ ይግባኝን አስመልክቶ ትንሽ ማሻሻያ አድርጐበታል፡፡

[91] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 34፡፡

[92] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 36፡፡

*የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡*[93] *ይህ አዋጅ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን በማቀፍ የተደራጀ ሲሆን ስለግብር ይግባኝ ጉዳይም የሚያወሱ ጥቂት ድንጋጌዎች ነበሩት፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ግብር ከፋዩ ይግባኝ የማለት መብት የነበረው መሆኑን፣*[94] *ይግባኝ ለማለት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣*[95] *ስለይግባኝ ሰሚው ኮሚቴ አደረጃጀት፣*[96] *ስለይግባኝ ማመልከቻ አቀራረብና*[97] *ስለማስረዳት ሸክም*[98] *የሚደነግጉ ነበሩ፡፡*

*በዚህ ሕግ አንቀጽ 27 መሠረት ማናቸውም ግብር ከፋይ በተሰጠው የግብር ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሳኔው ከተገለፀለት አንስቶ ባሉት ሠላሳ ቀኖች ውስጥ ለወረዳ ግብር ይግባኝ ኮሚቴ ይግባኝ ለማቅረብ መብት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በግብር ውሳኔው ላይ ቅሬታ ያደረበት ግብር ከፋይ በዚህ መብቱ ሊሠራበት የሚችለው እንዲከፍል ከተወሰነው ግብር ላይ 75% በመያዣ ለታክስ አስገቢው መሥሪያ ቤት የከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡*[99] *ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የወረዳው ግብር ይግባኝ ኮሚቴ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ትርጉም የተሳሳተ ነው ብሎ የማይቀበለው ከሆነ ኮሚቴው የወሰነበትን ግብር በሙሉ ከፍሎ ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀን ውስጥ ይግባኙን ለአውራጃው ፍ/ቤት የማቅረብ መብት ነበረው፡፡*[100] *ይግባኝ የሚቀርብለት የአውራጃው ፍ/ቤትም በሕግ ትርጉም ረገድ ስህተት ያለ ሆኖ ሲያገኘው ይህንኑ ስህተት ብቻ አቃንቶ ኮሚቴው ውሳኔ እንዲሰጥበት መልሶ የሚልክለት ሲሆን የአውራጃው ፍ/ቤት ውሳኔም የመጨረሻ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡*[101] *እንዲሁም በ1968 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ*[102] *በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለማቅረብ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ የዚህ አዋጅ ዝርዝር ድንጋጌዎች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው አዋጅ (የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና ከእርሻ ገቢ የሚገኝ አዋጅ) ድንጋጌዎች ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ናቸው፡፡*[103]

*ከዚሁ ከደርግ ዘመነ-መንግሥት ሳንወጣ ሌላው የምንመለከተው አዋጅ በ1979 ዓ.ም የወጣውን የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ነው፡፡*[104] *በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የአገር ውስጥ ገቢ አስተዳደር በወሰነው የቴምብር ቀረጥ ሂሳብ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ አስተዳደሩ ውሳኔውን በጽሑፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ ከ21 ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚችል ተደንግጎ ነበር፡፡*[105] *በደርግ ዘመነ-*

---

93 *የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና በእርሻ ሥራ ገቢ ላይ ግብር ለማስከፈል የወጣ አዋጅ፣አዋጅ ቁጥር 77/1968፣ነጋሪት ጋዜጣ፣35ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19፡፡*

94 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 27(2)ን ይመልከቱ፡፡*

95 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 28፡፡*

96 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 29፡፡*

97 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 30፡፡*

98 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 31፡፡*

99 *ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 28፡፡*

100 *ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 34፡፡*

101 *ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 35፡፡*

102 *የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ፣አዋጅ ቁጥር 80/1968፣ነጋሪት ጋዜጣ፣35ኛ ዓመት፣ቁጥር 25፡፡*

103 *ዝኒ ከማሁ፣ ከአንቀጽ 9-12 ያሉትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ይመልከቱ፡፡*

104 *የቴምብር ቀረጥ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 334/1979፣ነጋሪት ጋዜጣ፣46ኛ ዓመት፣ቁጥር 25፡፡*

105 *ይግባኝን በተመለከተ ይህ አዋጅ የወሰደው አቋም ከዚህ በፊት የመረመርናቸው የሀገራችን የታክስ ሕጐች ከወሰዱት አቋም በእጅጉ የተለየ ነበር፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት አንድ ቅሬታ የገባው የቴምብር ቀረጥ ከፋይ ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለማቅረብ የሚችልበት ዕድል አልነበረውም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ*

መንግሥት ከወጡት የታክስ ሕጐች ውስጥ የታክስ ይግባኝን በሚመለከት ሳይጠቀስ የማይታለፈው ሌላው ሕግ በኢ.ሕ.ዴ.ሪ የመንግሥት ም/ቤት በ1982 ዓ.ም የወጣው የሽያጭ ታክስ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡[106] በዚህ ልዩ ድንጋጌ አንቀጽ 12 እንደተገለፀው የታክስ ባለሥልጣኑ በወሰነው ታክስ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ከተወሰነው ታክስ 75% በጥሬ ገንዘብ ለታክስ ባለሥልጣኑ በማስያዝ፣ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ይግባኝ የማቅረብ መብት ነበረው፡፡[107]

የደርግ መንግሥት በ1983 ዓ.ም ከሥልጣን መውረዱን ተከትሎ በሀገሪቱ የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ ነበር፡፡[108] ከ1983-1987 ዓ.ም ድረስ ሀገሪቱን ሲያስተዳድር የነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተለያዩ መሠረታዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ለውጦች ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የታክስ ሕጐችን በተመለከተ ግን አነስተኛ የጥገና ለውጥ ከማድረግ በስተቀር ቀድሞ የነበረውን የታክስ ሕግና ሥርዓት አልለወጠም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ የሽግግር ወቅትም ቢሆን የወጡት የታክስ ሕጐች ወይም ማሻሻያዎች የታክስ ይግባኝን አስመልክተው ድንጋጌዎችን ይዘው መውጣታቸው አልቀረም፡፡ ለአብነት ያህል በ1985 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ[109] በአንቀጽ 17 ሥር "የታክስ ባለሥልጣኑ በወሰነው ታክስ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ከተወሰነው ታክስ 50% በጥሬ ገንዘብ ለታክስ ባለሥልጣኑ በማስያዝ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለኮሚሲዮኑ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው" ሲል ደንግጎ ነበር፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ደግሞ በ1953 ዓ.ም በወጣው የገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) የተደነገጉትና የግብር ይግባኝን የሚገዙት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡

ይግባኙን ለከፍተኛው ፍ/ቤት ማቅረብ የሚጠበቅበት በቀደሙት ሕጐች እንደተደነገገው የግብር ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ሳይሆን በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነበር፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ይግባኝ ለማለት የሚፈልገው ሰው የአገር ውስጥ ገቢ አስተዳደር ከወሰነው ታክስ ውስጥ የተወሰነ መቶኛ አስቀድሞ ገቢ ማድረግ ወይም ማስያዝ እንደሚገባው አልተደነገገም ነበር፡፡ በአራተኛ ደረጃ ደግሞ የከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ሥልጣን በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ወይም  የፍሬ ነገር ጉዳዮችንም ጨምሮ ለማየት የሚችል መሆን አለመሆኑ በሕጉ አልተመለከተም ነበር፡፡

106 የሽያጭ ታክስ የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ፣ድንጋጌ ቁጥር 19/1982፣ነጋሪት ጋዜጣ፣ 49ኛ ዓመት፣ ቁጥር 11፡፡

107 ዝኒ ከማሁ፣የዚሁ ልዩ ድንጋጌ አንቀጽ 12 (3) ደግሞ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለ) ስለይግባኝ የተወሰኑ ድንጎጌዎች ለሽያጭ ታክስ ጉዳዮችም ተፈጻሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በ1953 ዓ.ም የወጣው የገቢ ግብር አዋጅ ስለይግባኝ አቀራረብ፣ ስለማስያዣ፣ ስለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር፣ ስለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች ሥልጣንና መሰል ጉዳዮች የደነገገው በ1982 ዓ.ም በወጣው የሽያጭ ታክስ ሕግ አፈጻፀም ላይ ለሚነሱ የግብር ይግባኝ ሥርዓት አካሄድና አፈጻፀም ተግባራዊ ይደረጋል ማለት ነው፡፡

108 Assefa Fiseha (2006), *Federalism and the Accomodation of Diversity in Ethiopia*,Wolf Legal Publishers, the Netherlands, ከገጽ 44-52 ያለውን ሐተታ ይመልከቱ፡፡

109 የሽያጭና ኤክሳይ ታክስ አዋጅ፣አዋጅ ቁጥር 68/1985፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣52ኛ ዓመት፣ ቁጥር 61፡፡

## 3. በኢፌዲሪ የታክስ ከፋይ ቅሬታዎች አፈታት ሥርዓት

### 3.1 የመንደርደሪያ ሐሳቦች

በ1987 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት (ከዚህ በኋላ ሕገ-መንግሥቱ እየተባለ የሚጠቀስ) ከታወጀ በኋላ የሀገራችን የመንግሥት አወቃቀር ፌዴራላዊ መሆኑ ታወጀ::[110] ይኸው ሕገ-መንግሥት ዘጠኝ የክልል መንግሥታት[111] መቋቋማቸውን ከመደንገጉም በላይ በፌዴራል መንግሥቱና በክልል መንግሥታት መካከል ሕግ የማውጣት፣ ሕግ የማስፈፀምና የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል የተደረገ መሆኑን አረጋገጠ::[112] በፌዴራል ሥርዓት ውስጥ የሚደረግ የሥልጣን ክፍፍል ትርጉም የሚኖረው ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ክፍፍል እውን ሲሆን ብቻ በመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥትም በፌደራል መንግሥት እና በክልሎች መካከል ሊኖር የሚገባውን የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ደንግጓል::[113] በዚህም መሠረት ለፌዴራል መንግሥት ብቻ የተሰጡ የታክስ ሥልጣናት፣[114] ለክልሎች ብቻ የተሰጡ የታክስ ሥልጣናት[115]፣ ለፌዴራል መንግሥቱና ለክልሎች በጋራ የተሰጡ የታክስ ሥልጣናትና[116] ለየትኛውም የመንግሥት እርከን ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣናት (undesignated powers of taxation)[117] ተለይተው ተገልፀዋል:: ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የክልል መንግሥታት ለእነሱ ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣናት ላይ ታክስ ለመጣልና ለመሰብሰብ የሚያስችሏቸውን ሕጐች የማውጣት ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ነው:: በዚህም ምክንያት በራሳቸው ክልል በታክስ ከፋዮችና በታክስ አስገቢ ባለሥልጣናት መካከል የሚነሱትን አለመግባባቶች ለመፍታት የሚያስችሏቸውን ሥርዓቶችም አብረው የመዘርጋት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን አላቸው::[118] ያም ሆኖ በኢትዮጵያ የተዋቀሩት ክልሎች የራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ የታክስ ፖሊሲዎች ሲነድፉና የታክስ ሕግ ሲያወጡ አልተስተዋሉም:: ይልቁንም ክልሎቹ በተቋቋሙበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የፌዴራል መንግሥት ሲገለገልባቸው የነበሩትን የታክስ ሕጐች እነሱም ሲገለገሉባቸው ነበር::[119]

የፌዴራል መንግሥት ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ነድፎ በመንቀሳቀስ[120] በ1994 ዓ.ም እና 1995 ዓ.ም ዋና ዋናዎቹን የሀገሪቱን የታክስ ሕጐች ተግባራዊ አድርጓል::[121] ከዚህ ጊዜ በኋላም ቢሆን የክልል መንግሥታት

---

[110] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 50::

[111] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 47::

[112] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 50::

[113] ዝኒ ከማሁ፣ከአንቀጽ 95-100 ያሉትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይመልከቱ::

[114] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 96::

[115] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 97::

[116] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 98::

[117] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 99::

[118] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 51ን እና 52ን ይመልከቱ::

[119] Solomon Nigussie,*Fiscal Federalism in the Ethiopian Ethnic Based Federal System*,Wolf Legal Publishers,the Netherlands, 2006፣ ከገጽ 124-140 ይመልከቱ፤Taddese Lencho, '*Income Tax Assignment under the Ethiopian Constitution: Issues to Worry About*,' *Mizan Law Review*, Vol. 4,N 1, March 2010፣ ገጽ 45 ይመልከቱ::

[120] Alemayehu Geda, ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰ፣ ከገጽ 188-214 ያለውን ይመልከቱ::

[121] እነዚህም የገቢ ግብር አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ የቴምብር ቀረጥ ሕግ አዋጅ፤ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና የመሳሰሉት ናቸው::

ሕገ-መንግሥቱ የሰጣቸውን ሕግ የማውጣት ሥልጣን ተጠቅመው የራሳቸውን የታክስ ሕጎች ከማውጣት ይልቅ የፌዴራል መንግሥት ካወጣቸው ሕጐች ጋር ሙሉ ተመሳሳይነት ያላቸውን ሕጎች ሥራ ላይ አውለዋል፡፡[122] አንዳንድ ክልሎች ደግሞ የፌደራል መንግሥትን የታክስ ሕጎች በአዋጅ ተቀብለዋቸዋል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ነው፡፡[123] በዚህ የክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ የፌዴራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ (ማለትም አዋጅ ቁጥር 286/1994) እጅግ አነስተኛ ማስተካከያ[124] ተደርጎበት በትግራይ ክልልም ተፈጻሚነት እንዳለው ተደንግጓል፡፡[125]

ከዚህ በላይ ከተደረጉት ገለጻዎች መገንዘብ የሚቻለው ቁምነገር በኢትዮጵያ ውስጥ በፌደራል መንግሥት የታክስ ሕጎችና በክልል መንግሥታት የታክስ ሕጐች መካከል መሠረታዊ ልዩነት ስላልተፈጠረ የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚፈቱበት ሕጋዊ ሥርዓትም መሠረታዊ የሆነ ልዩነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አሁን በመላ ሀገሪቱ የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚያስተናግዱባቸው ተቋማት ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ፣ የግብር ይግባኝ ጉባኤና መደበኛ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው በእያንዳንዱ የግብር ቅሬታ ማስተናገጃ መዋቅር ሥር ያለውን የታክስ ከፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት ነው፡፡

### 3.2. የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች አጣሪ ኮሚቴ ስለሚፈታበት ሥርዓት[126]

የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በታክስ ከፋዮች ላይ የሚያሳድረውን ቅሬታ ለማረም ውስጣዊና[127]ውጫዊ[128] የመቆጣጠሪያ ሥልቶች (internal and external controlling

---

[122] በዚህ ረገድ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የኦሮሚያ ክልል የገቢ ግብር አዋጅ ነው፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር የገቢ ግብር አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 74/1995፣ መገለተ ኦሮሚያ፣ 9ኛ ዓመት፣ ቁጥር 12፡፡ ይህ አዋጅ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ከፌደራሉ የገቢ ግብር አዋጅ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ሌላው ቀርቶ በአናቅጽ አቀማመጥና ብዛት እንኳን ሁለቱ ሕጎች አንድ ናቸው፡፡

[123] የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 68/1995፣ ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ፣11ኛ ዓመት፣ቁጥር 10፣

[124] ዝኒ ከማሁ፤የተደረጉትን ማስተካከያዎች ለመረዳት የአዋጁን አንቀጽ 3 ይመልከቱ፡፡

[125] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 2፡፡

[126] በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ለምናደርጋቸው ገለጻዎች ተደጋግመው የሚጠቀሱት የገቢ ግብር አዋጁ (ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ) ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የሌሎቹ ታክስ ሕጎቻችን ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚመሳሰሉ በመሆናቸው እነሱን እየደጋገሙ መጥቀስ አንባቢን የሚያሰለች ከመሆኑም በላይ የጽሁፉንም ውበት ይቀንሰዋል፡፡ ስለሆነም ክቡራን አንባቢያን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣በማስታወሻ ቁጥር 41 የተጠቀሰ፣ ከአንቀጽ 40-42 ያሉትን ድንጋጌዎች፣በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 42 የተጠቀሰ፣ ከ18-20 ያሉትን ድንጋጌዎች፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 43 የተጠቀሰ፣ ከ15-17፣ ያሉትን ድንጋጌዎች፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 622/2001፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 27 በአንቀጽ 87 የተደነገጉትን እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣ ያወጣውን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያ መመሪያና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ቡድን ማቋቋሚያና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 45/2002 ይመልከቱ( ያልታተሙ ናቸው)፡፡

[127] ይህንን ጉዳይ ይበልጥ ለመገንዘብ የሚከተለውን ሥራ መልከቱ፡- N.K.Jayakumar (2005), *Administrative Law*, New Delhi፡ Prentice-Hall of India Private Limited. ይህ የቁጥጥር ስልት የሚያመለክተው በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በየደረጃው የሚደረገውን ቁጥጥር ነው፡፡ ለምሳሌ ያክል በአንድ የሚኒስቴር መ/ቤት ሚኒስትሩ የመምሪያ ኃላፊውን

mechanisms) በሕግ ማቋቋም የግድ አስፈላጊ ነው። በሀገራችን የታክስ ሕጐች እውቅና የተሰጠው አጣሪ ኮሚቴ ውስጣዊ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ነው።

አሁን በሥራ ላይ ያሉት የታክስ ሕጐቻችን ከታወጁ ወዲህ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን *አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ* ተብሎ ለሚጠራውና በሕግ ዕውቅና ለተሰጠው አካል የማቅረብ መብት አለው። ይህ አጣሪ ኮሚቴ በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል ደረጃ ተቋቁሟል። በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው አባላት በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ አቅራቢነት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንደሚሰየሙ የገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 104 ይደነግጋል።[129] የገቢ ግብር አዋጅ የፌዴራል መንግሥት ሕግ እንደመሆኑ መጠን አጣሪ ኮሚቴዎች በክልሎች እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው መደንገግ የማይገባው ቢሆንም ይኸው የአዋጁ አንቀጽ በክልል ደረጃ የአጣሪ ኮሚቴው አባላት አግባብ ባለው የክልል ባለሥልጣን እንደሚሰየሙ ያረጋግጣል።[130] የክልሎቹን የገቢ ግብር ሕግጋት ስንመለከትም የፌደራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ከሚደነግገው ጋር በተጣጣመ መልኩ ደንግገው እናገኛቸዋለን።[131] ለምሳሌ ያህል የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ[132] አንቀጽ 104 የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው አባላት በየደረጃው በሚገኙ የግብር ባለሥልጣን ኃላፊዎች አቅራቢነት እንደአግባብነቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ፣ በዞን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ኃላፊ፣ በወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም በከተሞች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ኃላፊ ይሰየማሉ በማለት ይደነግጋል።

በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ በግልጽ እንተደነገገው የአጣሪ ኮሚቴው ተጠሪነት ለሚመለከተው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሆኖ፣[133] የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 105 እንደሚያትተው የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪ እንዲያደርግ እና የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ተቀብሎ ለመመርምርና የውሳኔ ሓሳብ ለማቅረብ የሚያስችል ሥልጣን አለው። ይህንን ሥልጣኑን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻለውም ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውም የጽሑፍ ማስረጃዎች መሰብሰብ እንዲችል፣ በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከግብር አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውም ሰው የመጥራትና የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሰጠው የግብር ውሳኔ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ሕጉን ተከትሎ የተሰጠ

የሚቆጣጠር ሲሆን፣ የመምሪያ ኃላፊው ደግሞ ከእርሱ በታች ያለውን ባለሥልጣን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት ማለት ነው።

128 ስያሜው እንደሚያመለክተው ይህ ቁጥጥር ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ባሉ የመንግሥት ተቋማት የሚደረግ ቁጥጥር ነው። በአንድ የመንግሥት አስተዳደር መሥሪያ ቤት ላይ ውጫዊ ቁጥጥር በማድረግ በሰፊው የሚታወቁት ፍርድ ቤቶች፣ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ መገናኛ ብዙሀን፣ የጸረ-ሙስና ኮሚሽንና የመሳሰሉት ናቸው።

129 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ።

130 ዝኒ ከማሁ

131 የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የጋምቤላ እና የትግራይ ክልሎች የገቢ ግብር አዋጆች የፌደራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ከሚደነግገው የተለየ አቋም የላቸውም።

132 የኦሮሚያ ክልል የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 122 የተጠቀሰ።

133 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 104። መቀጫ ማንሳትን በተመለከተ መጀመሪያ በ1994 ዓ.ም አንድ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ወጥቶ የነበረ ሲሆን፣ በ1996 ዓ.ም ይኸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መመሪያ ቁጥር 5/1996ን አሻሽሎ አውጥቷል።

መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡[134] በተጨማሪም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በግብር ከፋዩ ላይ የሚጣለውን አስተደዳደራዊ መቀጫ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲነሳ ለማድረግ እንደሚችል በዚሁ ሕግ ተደንግጓል፡፡[135]

በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴው የሚያቀርበው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ሆኖም ግን ቅሬታው መቅረብ የሚኖርበት ታክስ ከፋዩ የግብር ውሳኔ በደረሰው አሥር ቀናት ውስጥ ብቻ ነው፡፡[136] በዚህ ረገድ በሀገራችን ከሚሠራባቸው የታክስ ሕጎች ውስጥ ለየት ያለ አቋም የወሰዱት በ2001 ዓ.ም የወጣው የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ[137] እና በ2001 ዓ.ም የወጣው የጉምሩክ አዋጅ ናቸው፡፡[138] ምክንያቱም በቴምብር ቀረጥ አዋጅ (ማሻሻያ) አንቀጽ 2(2) በማያሻማ ሁኔታ እንደተደነገገው ማንኛውም በቴምብር ቀረጥ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴው የሚያቀርበው ውሳኔው *በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ነው*፡፡ (አንክሮ የጸሐፊው ነው)፡፡ በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 87(2) ሥር ደግሞ ቀረጡን በተቃውሞ የከፈለ ሰው *ክፍያ በፈጸመ በ15 ቀናት ውስጥ* ቅሬታውን በባለስልጣኑ ለተቋቋመው አቤቱታ አጣሪ ቡድን ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ አዋጆች ውስጥ የተመለከተው ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ የአሥር ቀን ገደብ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ዋና ጥያቄ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠው የአስር ቀን የጊዜ ገደብ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

እንደ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች አመለካከት ከሆነ በሕጉ የተመለከተው የአሥር ቀን ገደብ በቂ ነው የሚል ነው፡፡[139] ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት የታክስ ኦዲተሩ ገና ሥራውን ሲጀምር ግብር ከፋዩን አሳውቆ በእያንዳንዷ ሰነድ ላይ እየተወያዩ ግብሩ ስለሚወሰን ለግብር ከፋዩ እንግዳ የሚሆን ነገር ሊኖር አይችልም የሚል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ወደ አጣሪ ኮሚቴው ከመምጣቱ በፊት ታክሱን በሚወስነው የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛና በታክስ ከፋዩ መካከል *የመተማመን ውይይት* (exit conference) ስለሚደረግ ታክስ ከፋዩ ለጉዳዩ እንግዳ ስለማይሆን ግብር ከፋዩ በሕጉ በተቀመጠው የአሥር ቀን ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴው ለማቅረብ እንደማያዳግተው የግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ይገልፃሉ፡፡[140]

በአንፃሩ ደግሞ ቅሬታ የተሰማውን ታክስ ከፋይ አቤቱታ የማቅረብና የመስማት መሠረታዊ መብት እውን ለማድረግ ይህ የቀን ገደብ በመጠኑ ረዘም ቢል መልካም

---

[134] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 105፡፡

[135] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 106፡፡

[136] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 105(2)፡፡

[137] የቴምብር ቀረጥ (ማሻሻያ) አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 612/2001፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፡፡

[138] የጉምሩክ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 126 የተጠቀሰ፡፡

[139] ቃለ መጠይቅ፣ ከአቶ ጌታቸው ታደሰ ጋር የተደረገ፣ አቶ ጌታቸው ታደሰ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የትምህርት ድጋፍ ቡድን አስተባባሪና የአጣሪ ኮሚቴ አባል፣ ሐምሌ 03 ቀን 2005 ዓ.ም፡፡

[140] ይሁን እንጂ እንዲህ ያለው የመተማመን ውይይት የሚደረገው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ መሆኑን በዚህ ረገድ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፤ Misganaw Gashaw, ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰ፣ ገጽ 41፡፡

ስለመሆኑ የሚቀርቡ አስተያየቶች አሉ፡፡[141] በሌሎች *ሀገራት* ያለው ተሞክሮ ይህንን አስተያየት የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ ያህል በብራዚል የሪዮ ዲ ጀኔሮ ግዛት የታክስ ሕግ በግልጽ እንደሚደነግገው ማንኛውም የታክስ ውሳኔ የደረሰው ታክስ ከፋይ በውሳኔው ላይ ተቃውሞ ካለው ይህንን ተቃውሞውን ውሳኔውን ላስተላለፈው አካል የሚያቀርበው ውሳኔው ከደረሰው ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ነው፡፡[142] በአሜሪካ ደግሞ *በሀገር ውስጥ የገቢ አገልግሎት መ/ቤት* (Internal Revenue Service) የታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለዚሁ መ/ቤት ቅሬታ ሰሚ አካል የሚያቀርበው የታክስ ውሳኔው በደረሰው በ90 ቀናት ውስጥ ነው፡፡ ታክስ ከፋዩ የሚኖረው ከአሜሪካ ውጭ የሆነ እንደሆነ በውሳኔው ላይ የሚኖረውን ቅሬታ ውሳኔው በተሰጠው በ150 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡[143] በቻይና የታክስ ሰብሳቢው ባለሥልጣን በሚሰጠው የግብር ውሳኔ ላይ ቅሬታ ለሚመለከተው አካል የሚቀርበው ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ነው፡፡[144] በግብፅ እ.ኤ.አ በ2005 የወጣው የሀገሪቱ ገቢ ግብር ሕግ አንቀጽ 116 *መሠረት* የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በሚሰጠው የታክስ ውሳኔ ያልተስማማ ሰው ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ መብት አለው፡፡[145] በአጠቃላይ ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (Organization for Economic Cooperation and Development) ያደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የጊዜው ገደብ ከሀገር ሀገር የሚለያይ ቢሆንም፣ታክስ ከፋዮች እንዲህ ዓይነቱን ቅሬታ የሚያቀርቡበት ጊዜ ከ21 እስከ 90 ባሉት ቀናት ውስጥ ነው፡፡[146]

በኢትዮጵያ የታክስ ከፋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ውስጥ የተደነገገው የአሥር ቀናት የጊዜ ገደብ ከዓለም ዓቀፉ እውነታ ጋር ስለማይጣጣም ተገቢው ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል ብሎ መከራከር አግባብነት አለው፡፡ በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አመለካከትም አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ውሳኔው ላይ ያለውን ቅሬታ ለማሰማት እንዲችል ዕድል ከተሰጠው በኋላ አቤቱታውን የሚያቀርብበትን ጊዜ ከመጠን በላይ አጭር ማድረግ በአንድ እጅ የተሰጠውን መብት በሌላ እጅ እንደመንፈግ የሚቆጠር ነው፡፡ በሕጉ የተገለፀው የአሥር ቀን ገደብ

---

141 ቃለመጠይቅ ከዶ/ር ታደሰ ሌንጮ ጋር (ሐምሌ 2 ቀን 2005 ዓ.ም)፡፡ ዶ/ር ታደሰ ሌንጮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር ሲሆኑ በታክስ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን የሚሠሩ ናቸው፡፡

142 Marcelo Habib Garvalho (2013), Tax Appleal Processes in the Treasury Secretariat of the State of Rio De Jeneiro and the IUnternal Revenue Service, School of Business and Public Mnagement IBI-The Institute of Birazilian Issues, Minerva Program, Fall 2013, Washington D.C, available at <www.gwu.edu/~ibi/minerva/Fall2013/Marcelo_Carvalho.pdf>, accessed on 29 September 2014፣ ገጽ 7 ላይ ይመልከቱ፡፡

143 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 24፡፡

144 Fuli Cao, Corporate Income Tax Law and Practice in the People's Republic of China, Oxford University Press, 2011,ገጽ.395.

145 የግብጽን የገቢ ግብር ሕግ ይመልከቱ፤ Income Tax Law, 2005, available at <www.mof.gov.eg/MOFGallerySource/english/IncomeTaxLaw.pdf>, accessed on 29 September 2014.

146 David Crowaford, Detailed Guidelines for Improved Tax Administration in Latin America and the Caribbean,Chapter 11, UASAID's Leadership in Management, 2013, available at <www.usaid.gov/where-we.../latin-american...caribbean/tax-administration>, accessed on 30 September 2014 ፣ ገጽ 20፡፡

ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ በጣም አጭር ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ የሀገራችን ታክስ ከፋዮች ስለታክስ ሕጎቻችን በቂ ዕውቀት የሌላቸው፣ በመስኩ ሙያ ያላቸውን ሰዎች የማያማክሩ እና ተገቢውን እርምጃ በተገቢው ጊዜና ቦታ መውሰድ የማይችሉ ስለሆኑ ለአጣሪ ኮሚቴው አቤቱታቸውን የሚያዘጋጅላቸው ባለሙያ መፈለግ፣ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችና መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናቀር ጊዜ ይጠይቃቸዋል፡፡ በመሆኑም የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅና የጉምሩክ አዋጅ እንዳደረጉት ሁሉ፣ በዚህ ረገድ አስፈላጊው ጥናት  ተደርጎ የአሥር ቀኑ የጊዜ ገደብ ወደ ሃያ ወይም ሠላሳ ቀን ከፍ ቢል ታክስ ከፋዩን ማኅበረሰብ የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ በመንግሥት ገቢ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 105(3) በግልጽ እንደተደነገገው የአጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ የመጨረሻ አይደለም፡፡ ይልቁንም አጣሪ ኮሚቴው በቀረበለት ጉዳይ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ከአሳለፈ በኋላ ይህንኑ የውሳኔ ሓሳብ ለሚመለከተው የግብር አስገቢ ባለሥልጣን ኃላፊ ውሳኔ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊም የቀረበለትን የውሳኔ ሓሳብ እንዳለ ሊያጸድቀው፣ ውድቅ ሊያደርገው ወይም በውሳኔ ሓሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለጽ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡

ከዚሁ ከታክስ አጣሪ ኮሚቴ ሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ዐብይ ጥያቄ የታክስ አጣሪውን ኮሚቴ የሥልጣን ወሰን የሚመለከት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የታክስ አጣሪ ኮሚቴው የሚመለከተው ከታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥያቄዎች ብቻ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ለምሳሌ ያህል አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ፣ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት ገቢ የማያመነጭ ግለሰብ፣ ለኢትዮጵያ መንግሥት የገቢ ግብር እንዲከፍል ቢጠየቅና ይህ ግለሰብ የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕግ በእኔ ላይ ተፈጻሚነት የለውም የሚል ክርክር ቢያነሳ አጣሪ ኮሚቴው እንዲህ ያለውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመመርመርና እልባት ለመስጠት ሥልጣን አለው ብሎ በድፍረት ለመናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ እዚህ ላይ እንዲህ ዓይነቶቹን ጉዳዮች በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ይዞ መሄድ አይቻልም ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ታክስ ጉዳዮችን ተቀብለው የሚያስተናግዱት ከግብር ይግባኝ ጉባኤ ላይ ይግባኝ ሲባል በመሆኑ እንዲህ ያለውን ጉዳይ በቀጥታ ያስተናግዳሉ ብሎ ለማሰብ ይከብዳል፡፡

ይህንንም አስመልክቶ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ቃለመጠይቅ ያደረገላቸው አቶ ጌታቸው ታደሰ (የአጣሪ ኮሚቴ አባል)፣ እንዲህ ዓይነት ከባድ የሕግ ጥያቄ ሲያጋጥም ኮሚቴው እንደማይመለከተው አረጋግጠዋል፡፡[147] ይልቁንም እንዲህ ዓይነት ወሳኝ የሆነ የሕግ ጥያቄ በሚያጋጥምበት ጊዜ ጥያቄው በዋናው መ/ቤት ተቋቁሞ ለነበረው የቴክኒክ ኮሚቴ ተብሎ ይጠራ ለነበረው አካል እንደሚተላልፍ አስረድተዋል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴውም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የውሳኔ ሓሳቡን ለባሥልጣኑ ዳይሬክተር እንደሚያቀርብ አቶ ጌታቸው ጨምረው አረጋግጠዋል፡፡[148] ይሁን እንጂ ይህ የቴክኒክ ኮሚቴ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የተቋቋመ እንጂ በዋና ዋናዎቹ የታክስ ሕጎች እውቅና ያልተሰጠው ስለሆነ የሚሰጠው ውሳኔውም የሕግ መሠረት ያለው ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ስለሆነም፣ የአጣሪው ኮሚቴ አባላት በቂ ዕውቀት፣ ልምድና ሥነ-ምግባር ያላቸው ግለሰቦች እንዲሆኑ እስከተደረገ ድረስ ማናቸውንም ቅሬታዎች የማየትና አስተያየት የማቅረብ ሥልጣን ቢሰጣቸው ጠቀሜታ እንደሚኖረው የዚህ ጸሀፊ እምነት ነው፡፡[149]

---

[147] ጌታቸው ታደሰ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 139 የተጠቀሰ፡፡

[148] ዝኒ ከማሁ፡፡

[149] አንዳንድ የሕግና ከሕግ ሙያም ውጭ የሆኑ ባለሙያዎች የቴክኒክ ኮሚቴ ተብሎ ይጠራ የነበረው አካል የሕግ መሠረት ያለው ተቋም ነው ብለው ሲከራከሩ ጸሐፊው ለመገንዘብ ችሏል፡፡

ስለ አጣሪ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር ስንነጋገር የሚነሳው ሌላ ነጥብ የአጣሪ ኮሚቴው ገለልተኛ የመሆን አለመሆን ጉዳይ ነው፡፡ በመሠረቱ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭ አካላት ከሚተቹባቸው ጉዳዮች አንዱ ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ አይሰጡም በሚል ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይም ስንመጣ አንዳንድ ጥናቶች[150] እንደሚያመለክቱት የኮሚቴው አባላት በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ የሚሾሙ እንደመሆናቸውና ተጠሪነታቸውም ለዚሁ ኃላፊ እንደመሆኑ ገለልተኝነታቸው በጣም አጠራጣሪ ነው የሚል አመለካከት አለ፡፡ ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል በተደረገ የምክክር ስብሰባ ታክስ ከፋዮቹ የአጣሪ ኮሚቴው አባላት ለታክስ ባለሥልጣኑ እንደሚያደሉ ገልፀዋል፡፡[151] ይህ ጸሐፊ ጥያቄ ያቀረበላቸው የአጣሪ ኮሚቴ አባል ግን "ሥራችን በምንሠራበት ጊዜ ምንም ዓይነት ጫና ተፈጥሮብን አያውቅም፤ ሥራችንን የምንሠራውም በፍፁም ገለልተኝነት ነው፣ ይልቁንም ቅሬታውን የሚያቀርበው ታክስ ከፋይ ቀድሞውንም ቢሆን አጣሪ ኮሚቴው ገለልተኛ አይደለም የሚል አመለካከት ይዞ ነው የሚመጣው" ብለዋል፡፡[152]

## 3.3 የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች በግብር ይግባኝ ጉባኤ ስለሚፈቱበት ሥርዓት[153]

ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ የወጡትን የታክስ ሕጎች በዳሰስንበት ጊዜ እንደተረዳነው የግብር ይግባኝ ጉባኤ ይቋቋም የነበረው እራሱን በቻለ ሕግ ሳይሆን ስለታክስ ጉዳዮች በሚደነግጉ ሕጐች አማካይነት ነበር፡፡ ነገር ግን በ1993 ዓ.ም የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ የሚባል ተቋም በአዋጅ ቁጥር 233/1993[154] ራሱን ችሎ ተቋቁሞ ነበር፡፡ ይህ አዋጅ ብዙም ሳይቆይ በ1994 ዓ.ም በወጣው የገቢ ግብር አዋጅ[155] ስለተሻረ የግብር ይግባኝ ጉባኤውም በዚሁ

ለምሳሌ ያህል የዚህ ጸሁፍ መነሻ ጥናት በግሉ ሴክተርና በመንግሥት መካከል ለሚደረገው ውይይት መነሻ ሓሳብ ሆኖ በዚህ ጸሐፊ በመድረክ ቀርቦ በነበረበት ጊዜ በርካታ ግለሰቦች የቴክኒክ ኮሚቴው ሕጋዊ መሠረት ያለው ተቋም ነው በማለት አጥብቀው ሲከራከሩ እንደነበር ጸሐፊው ተረድቷል፡፡ ይህ ተቋም በአሁኑ ጊዜ (በመስከረም 2007 ዓ.ም) አገልግሎት ከመስጠት ታግዷል፡፡

150 Misganaw Gashaw, ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰ፣ገጽ 43፡፡

151 ዝኒ ከማሁ፡፡

152 አቶ ጌታቸው ታደሰ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 139 የተጠቀሰ፡፡

153 በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ለምናደርጋቸው ገለጻዎች ተደጋግመው የሚጠቀሱት የገቢ ግብር አዋጁ (ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ) ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የሌሎቹ ታክስ ሕጎቻችን ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚመሳሰሉ በመሆናቸው እነሱን እየደጋገሙ መጥቀስ አንባቢን የሚያሰለች ከመሆኑም በላይ የጽሁፉንም ውበት ይቀንሰዋል፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ከገቢ ግብር አዋጁ ውጭ ያሉት የታክስ ሕጎቻችን ይግባኝን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች በሌሎች የታክስ ክርክሮችም ተፈጻሚነት እንዳላቸው አመላክተዋልና ነው፡፡ ስለሆነም አንባቢያን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 45 የተጠቀሰ፣ ከአንቀጽ 43-44 ያሉትን ድንጋጌዎች፣በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 46 የተጠቀሰ፣ ከ21-22 ያሉትን ድንጋጌዎች፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 47 የተጠቀሰ፣ ከ18-19 ያሉትን ድንጋጌዎች፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 126 የተጠቀሰ፣ በአንቀጽ 87 የተደነገገውን እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡

154 የፌዴራል ግብር ይግባኝ ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 233/1993፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18፡፡

155 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰ፡፡

በኋለኛው አዋጅ እንደገና ለመቋቋም ቻለ፡፡[156] አሁን በሥራ ያለው የግብር ይግባኝ ጉባኤም ሥልጣኑን ያገኘውና ሥራውንም የሚሠራው በዚህ አዋጅ መሠረት ነው፡፡

### 3.3.1 የግብር ይግባኝ ጉባኤው አደረጃጀት

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 113 እንደተመለከተው የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች በፌዴራል መንግሥት እና በክልል ደረጃ፣ በእያንዳንዱ ዞን ዋና ከተማና በእያንዳንዱ የወረዳ አስተዳደር ደረጃ እንደሚቋቋሙ ነው፡፡ ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ 113(2) እንደተገለፀው የሚመለከተው የክልል መንግሥት በማንኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙት አካባቢዎች የተለየ የይግባኝ ጉባኤ ማቋቋም አስፈላጊ አለመሆኑን ሲረዳ እነዚህ ቦታዎች በአቅራቢያው በተቋቋመ የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለማድረግ ይችላል፡፡[157] በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 113(3) እንደተመለከተው የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለፍትሕ ሚኒስትሩ፣ የከተማ መስተዳድሮች ይግባኝ ጉባኤዎች ደግሞ ተጠሪነታቸው ለየመስተዳድሩ ሥራ አስፈጻሚ፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብር ይግባኝ ጉባኤዎች ተጠሪነታቸው በየደረጃው ላሉ ሥራ አስፈጻሚ አካላት ነው፡፡[158] ለምሳሌ ያህል በኦሮሚያ ክልል ያለው የጉባኤዎች ተጠሪነት በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ሙሉ በሙሉ የተከተለ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡[159] የትግራይ ክልል የገቢ ግብር አዋጅም የፌደራል መንግሥትን የገቢ ግብር አዋጅ የተቀበለ በመሆኑ የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች አደረጃጀትም ሆነ ተጠሪነት የፌደራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ከደነገገው የሚለይ አይደለም፡፡[160]

ምን ጊዜም ቢሆን ስለአንድ ተቋም አደረጃደትና አሠራር ስንነጋገር ሁነኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ተቋሙን የሚያንቀሳቅሱት ሰዎች አመራረጥና አሰያየም ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሱ የሚችሉት መሠረታዊ  ጥያቄዎች የጉባኤው አባላት የሚሰየሙት በማን ነው? ሰዎቹ የሚሰየሙት በምን መለኪያ ነው? የአባላቱ ስብጥር የሚወሰነው በምን ሁኔታ ነው? የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለው የአዋጁ[161] አንቀጽ 114 ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት እንደ አግባብነቱ የፍትሕ ሚኒስትር፣ ወይም የከተማ

---

[156] ከዚህም በተጨማሪ በ1994 ዓ.ም እና ከዚያም ጊዜ በኋላ የወጡት ሌሎች የታክስ ሕጎች የዚህን ጉባኤ መቋቋም በግልጽ የደነገጉ ቢሆንም ስለጉባኤው ሥልጣን፣ ኃላፊነትና የአሠራር ሂደት ዝርዝር ድንጋጌዎችን ከማካተት ይልቅ ዝርዝር ድንጋጌዎችን በማካተት ወደተደራጀው የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ሲያመላክቱ ይስተዋላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በዋነኛነት በገቢ ግብር አዋጅ ሥር የተካተቱት ድንጋጌዎች የሚተነተኑ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሌሎች አዋጆችም ድንጋጌዎች ቢያንስ በግርጌ ማስታወሻ ይጠቀሳሉ፡፡

[157] ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ ሀገራችን የምትከተለው የፌዴራል ሥርዓት መሆኑን የዘነጋ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በክልል ደረጃ ምን ዓይነት የግብር ይግባኝ ጉባኤ ማቋቋምና በየትኛው ደረጃ መቋቋም እንዳለበት የመወሰኑ ሥልጣን የክልል መንግሥታትን እንጂ የፌዴራል መንግሥትን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም እንዲህ ያለ ድንጋጌ በዚህ ሕግ ውስጥ ማስቀመጥ ፈጽሞ ሕገ-መንግሥታዊ አይደለም፡፡

[158] ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ይህም ድንጋጌ የክልሎችን በራሳቸው ጉዳይ ሕግ የማውጣት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን የሚጻረር ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ክልሎች እራሳቸው የሚያቋቁሙት የግብር ይግባኝ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለማን እንደሚሆን መወሰን ያለባቸው እራሳቸው ናቸው እንጂ የፌደራል መንግሥት ሕግ አይደለም፡፡ ይህም የሚያመለክተው የገቢ ግብር አዋጁን ያረቀቀው አካል በሕገ-መንግሥቱ እውቅና የተሰጠውን የክልሎችን ሕግ የማውጣት ሥልጣን ቸል ያለው መሆኑን ነው፡፡

[159] የኦሮሚያ ክልል የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 122፣ የተጠቀሰ አንቀጽ 113 ይመልከቱ፡፡

[160] የትግራይ ክልል የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 123 የተጠቀሰ፡፡

[161] የገቢ ግብር አዋጅ፣ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፡፡

አስተዳድሮችና የክልል ሥራ አስፈጻሚ አካላት የግብር ይግባኝ ሰሚ አባላት የሚመረጡበትን መመዘኛ እና ስብጥር የሚወስን መመሪያ የማውጣት ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ በክልል ደረጃ ስላለው ሁኔታ በርግጠኝነት መናገር ባይቻልም በፍትሕ ሚኒስቴር ደረጃ ግን ይህ መመሪያ እስካሁን አልወጣም፡፡[162] በ1994 ዓ.ም የወጣው ሕግ ይህ መመሪያ መውጣት እንደሚኖርበት ደንግጎ ሳለ፣ ይህንን መምሪያ ለማውጣት ሥልጣን የተሰጠው አካል እስካሁን ድረስ መመሪያውን አለማውጣቱ አግባብ አይደለም፡፡ የመመሪያው አለመውጣት በግብር ይግባኝ ጉባኤ አባላት አሰያየም ላይ የራሱ ተፅዕኖ ማሳደሩ እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የጉባዔው አባላት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከፍትሕ ሚኒስትር፣ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከንግዱ ማኅበረሰብ የተውጣጡ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል የግብር ይግባኝ ጉባኤ አባል የነበሩ አንድ አባል ለዚህ ጸሐፊ እንዳረጋገጡለት በእያንዳንዱ ችሎት (panel) ከአምስቱ የችሎቱ አባላት ውስጥ አንዱ የንግዱ ማኅበረሰብ ተወካይ ነው፡፡[163] ይሁን እንጂ ጉባኤው በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚመጡ አባላትን ማካተቱ ገለልተኝነቱ አስተማማኝ እንዳይሆን ያደርገዋል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ራሱ በወሰነው የግብር ውሳኔ ላይ ታክስ ከፋዩ ይግባኝ በሚልበት ጊዜ የራሱን ሰዎች የሚልክ ከሆነ በራሱ ጉዳይ ዳኛ እየሆነ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ማንኛውንም በሙስና የተጠረጠረ ሠራተኛ ከሥራ ማባረር እንደሚችልና ውሳኔውም ይግባኝ የማይባልበት ውሳኔ መሆኑ በሕግ የተደነገገ ስለሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚመጡት የጉባኤው አባላት ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ ይሰጣሉ ብሎ መገመት እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡[164] የገንዘብና ኢኮነኖሚ ልማት ሚኒስቴርም የታክስ ከፋዩን መብቶች የሚያጣብቡ ወይም ደግሞ ሸክሙን የሚያከብዱ መመሪያዎችን የሚያወጣው እና አደናጋሪ በሆኑ የታክስ ጉዳዮች ላይ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማብራሪያና ትርጉም የሚሰጥ አካል ሆኖ ሳለ የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውስጥ ተሳትፎ ማድረጉ አግባብነት አለው ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባልተከፋፈል የአክሲዮን ድርሻ ላይ የገቢ ግብር ለመጣል ባሰበበት ወቅት የሕግ ምክር የጠየቀው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ነበር፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲህ ያለውን የገቢ ግብር ለመሰብሰብ እንደሚችል በደብዳቤ ስላረጋገጠለት ባለሥልጣኑ ግብር መሰብሰብ በመጀመሩ በባለሥልጣኑና በታክስ ከፋዮች መካከል እጅግ የከረረ አለመግባባት ተከስቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ግብር የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ቅሬታቸውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ባቀረቡበት ጊዜ ደግሞ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተቀጣሪዎች በግብር ይግባኙ ዳኝነት መንበር ላይ የግድ ተሰይመው

---

162 ከአቶ ዳዊት ተሾመ ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ፣ ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ.ም፣ ቃለ-ምልልሱን ባደረግንበት ጊዜ አቶ ዳዊት ተሾመ በፍትሕ ሚኒስቴር ሠራተኛ የነበሩ ሲሆኑ በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር ባለው የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ አባልና ሰብሳቢ ነበሩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ (በመስከረም 2007) ግን የሕግ አማካሪና ጠበቃ ናቸው፡፡

163 ዝኒ ከማሁ፡፡

164 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2008፣ እንደዚሁም ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ጥሩ ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚከተለውን ሥራ ይመልከቱ፡- Aron Degol and Abdulatif Kedir, 'Administrative Rulemaking in Ethiopia: Normative and Institutional Framework", *Mizan Law Review*, Vol.7, No. 1, September 2013፤ ከገጽ 1-28 ያለውን ይመልከቱ፡፡

ይገኛሉ፡፡[165] በመሆኑም ይግባኛቸውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ የሚያቀርቡ ታክስ ከፋዮች በግብር ይግባኝ ጉባኤው ላይ እምነት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ከተፈለገ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሠራተኞች በጉባኤው ውስጥ አባል ሊደረጉ አይገባም፡፡

በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 608/2001[166] በአንቀጽ 2(11)[167] እንደተደነገገው በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አባላት የንግዱን ማኅበረሰብ ተወካዮች ጨምሮ[168] በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ታዋቂነትና ታማኝነት፣ ባላቸው ጠቅላላና ልዩ ዕውቀት፣ እንዲሁም ከግብር እና ቀረጥ ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈፀሙ ሰዎች መካከል ተመርጠው ይሰየማሉ፡፡ የጉባኤው አባላት ከግብርና ቀረጥ ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈፀሙ ሰዎች መካከል ይመረጣሉ የሚለውን ሐረግ ገልብጠን (a contrario) ስንተረጉመው በሌሎች የኢኮኖሚ ወንጀሎችና በሙስና ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ግለሰቦች የግብር ይግባኝ ጉባኤ አባላት ሆነው እንዲመረጡ የማይከለከሉ መሆኑን ለመረዳት የሚያዳግት አይደለም፡፡ በዚህ ፀሐፊ አምነት ማንኛውንም ዓይነት የኢኮኖሚ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ ሰው በግብር ይግባኝ ጉባኤ አባልነት ሊሰየም አይገባውም፡፡

በአዋጁ[169]አንቀጽ 114(4) በግልጽ እንደተደነገገው እያንዳንዱ የግብር ይግባኝ ጉባኤ ከአንድ የበለጡ ችሎቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ችሎትም አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን ችሎቱም የራሱ ሊቀመንበር ከአባላቱ መካከል እንደሚመርጥ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ለግብር ይግባኝ ጉባኤው በአጠቃላይ አንድ ፕሬዝዳንት ሊኖረው እንደሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 114(4) ሥር ተመልክቷል፡፡

### 3.3.2 ለግብር ይግባኝ ጉባኤው አቤቱታ የማቅረብ መብት

ታክስ ከፋዮች የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በደል ፈጽሞብናል የሚል እምነት ካላቸው ቅሬታቸውን የማሰማት የማይገሰስ መብት አላቸው፡፡ ይህም በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥትና በዓለም አቀፍ ሰብኣዊ መብቶች ስምምነቶችም ጭምር የተረጋገጠ መሠረታዊ መብት ነው፡፡[170] በመሆኑም በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 107 እንደተደነገገው በማንኛውም ግብር አወሳሰን ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በሕግ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እስካሟላ ድረስ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ቅሬታውን የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሠረት ማንኛውም ታክስ ከፋይ የይግባኝ መብቱን ሊሠራበት የሚችለው ግን በሕጉ ውስጥ

---

[165] ይህ ጸሐፊ የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ ለውይይት ባቀረበበት ጊዜ ይህንን ችግር በምሬት ሲገልጹ የነበሩ ታክስ ከፋዮች እንደነበሩ ለመታዘብ ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጸሐፊው ይህንን የምርምር ሥራ በሰራበት ወቅት የሚ/ር መ/ቤቱ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ለባለስልጣን መ/ቤቱ የጻፈውን ደብዳቤ ለማንበብ እድል አግኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ስለ ጉዳዩ ዝርዝር ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚከተለውን የምርምር ሥራ ይመልከቱ፡-Taddese Lencho and Hanna Arayaselassie, '*Divided over Divideneds: The Recent Controversies over the Meaning and Scope of Dividends and Lessens from Comparative Experience*', in Taddese Lencho and Kyle Logue(eds.), Ethiopian Tax System: Some Contemporaray Issues and Problems, Ethiopian Business Law Series, Vol.VI,2014፤ ከገጽ 147-182፡፡

[166] የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 608/2001፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 15፡፡

[167] በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደተመለከተው የገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 114(1) ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል፡፡

[168] በተሻረው የገቢ ግብር ድንጋጌ( ማለትም በአንቀጽ 114(1)) ሥር ነጋዴዎች የግብር ይግባኝ ጉባኤ አባል እንዲሆኑ አልተፈቀደላቸውም ነበር፡፡

[169] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፡፡

[170] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 37፡፡

የተመለከቱትን ሁለት ጥብቅ ቅድመ ሁኔታዎች በአንድነት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የአንድ ታክስ ከፋይ የይግባኝ ማመልከቻ በግብር ይግባኝ ጉባኤ ተቀባይነት የሚኖረው ታክስ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የታክስ መጠን ሃምሳ በመቶ (50%) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ካስያዘ እና የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው ወይም በአጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ከቻለ ነው፡፡[171]

እነዚህ ሁለት የይግባኝ ቅድመ-ሁኔታዎች ከ1930ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ የታክስ ሥርዓት ውስጥ የነበሩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በሀገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ አቤቱታውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ለማቅረብ የፈለገ ታክስ ከፋይ አከራካሪ የሆነውን የግብር መጠን 50% ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን እንዲያስይዝ መገደዱ በመርህ ደረጃ የማያከራክር ቢመስልም በአተገባበር ግን አስቸጋሪ ነው፡፡[172] አንዳንድ የታክስ ውሳኔ የሚሰጡ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች ታክስ ከፋዩ ፈጽሞ ሊወጣው የማይችለውን ግብር ይጭኑበታል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ የይግባኝ መብቱን ለማስከበር የዚህን ግማሽ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ታክስ ከፋዩ ይህንን ግማሽ ገንዘብ ለማስያዝ ካልቻለ ግን የይግባኝ መብቱን ሳይወድ በግድ ያጣዋል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ያልተፈለገ ውጤት ለማስቀረት ሌሎች ሀገሮች በእኛ ሀገር ካለው ጥብቅ የይግባኝ ቅድመ-ሁኔታ በእጅጉ የተሻሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል በቻይና በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ይግባኙን ለታክስ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ባለሥልጣን ለማቅረብ የተወሰነበትን ታክስ ለመክፈል ካልቻለ ወይም ካልፈለገ ተቀባይነት ያለው የሰው ዋስ በማቅረብ ወይም የንብረት ዋስትና በማቅረብ ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡[173]

በኢትዮጵም የታክስ ከፋዩን የይግባኝ መብት እውን ለማድረግ አከራካሪ የሆነውን ግብር 50% በጥሬ ገንዘብ ብቻ ታክስ ከፋዩ እንዲከፍል ከማስገደድ ይልቅ ሌሎች ዘዴዎችንም በአማራጭነት መመልከት አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በጣም ከፍተኛ የሆነ ግብር እንዲከፍል የተደረገ ታክስ ከፋይ አከራካሪ የሆነውን ግብር 50% ከፍሎ አቤቱታውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ጥሬ ገንዘብ ከሌለው ከፍተኛ ችግር ይገጥመዋል፡፡ እንዲህ ያለው ታክስ ከፋይ አንድም ንብረቶቹን በዋስትና እንዲያስይዝ ቢፈቀድለት አልያም ደግሞ በገንዘብ ተቋማት በተለይም በባንኮች የሚሰጥ የገንዘብ ዋስትና ቦንድ (financial guarantee bond) እንዲያቀርብ ቢፈቀድለት ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ዋስትና ሕጉ ባስቀመጠው እጭር ጊዜ ውስጥ (በ30 ቀናት ውስጥ) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሚያስይዘውን ጥሬ ገንዘብ በማጣት የይግባኝ መብቱን የሚያጣውን ታክስ ከፋይ ይታደጋልና ነው፡፡

ወደ ሁለተኛው የይግባኝ ቅድመ-ሁኔታ (የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ) ስንመጣም አንዳንድ ነጥቦች አነጋጋሪ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህ የ30 ቀናት ጊዜ ገደብ አጭር ጊዜ በመሆኑ የይግባኝ ባዮችን መብት የሚያጣብብ ነው የሚል አስተያየት አለ፡፡ በአንፃሩ

---

[171] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 107፡፡

[172] ይህ ችግር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ችግር እንደሆነ አንዳንድ የሀገራችን ምሁራን አበክረው አሳስበው ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ በአንድ ወቅት ባቀረቡት ጽሁፍ የችግሩን አሳሳቢነት ገልፀው ነበር፣ጥላሁን ተሾመ፣ *'የሕግ የበላይነትና ልማት በኢትዮጵያ፡ ዛሬና የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት'*፣ ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ፡ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ ላይ የቀረበ ጽሁፍ፣1996 ዓ.ም፣ገጽ 263፡፡ ይህን የፕሮፌሰር ጥላሁን ስጋት አቶ ዳዊት ተሾመና ዶ/ር ታደሰ ሌንጮም እንደሚጋሩት የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ቃለመጠይቅ ባደረገላቸው ጊዜ ለመገንዘብ ችሏል፡፡

[173] Fuli Cao፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 144 የተጠቀሰ፣ ከገጽ 395-396 ያለውን ይመልከቱ፡፡

ደግሞ እስካሁንም በወጡት የግብርና ታክስ ሕጐቻችን የተመለከተው የጊዜ ገደብ 30 ቀን በመሆኑና ይህ አዋጅ አዲስ ነገር ይዞ ስላልመጣ የ30 ቀኑ የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ መቀጠሉ ምንም የሚያመጣው ችግር የለም የሚል አስተያየት የሚሰጡ ወገኖች አሉ። እንደዚህ ጸሐፊ አመለካከት ይህ የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ የይግባኝ አቤቱታን በሚገባ አዘጋጅቶና በማስረጃ ደግፎ[174] ለማቅረብ የሚያንስ ይመስላል። ነገር ግን ለዚህ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ማግኘት ይቻል ዘንድ እስካሁን በነበረው ሁኔታ ምን ያህል ግብር ከፋዮች ቀኑ በማጠሩ ምክንያት ይግባኞቻቸውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ሳያቀርቡ የቀሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ተግባራዊ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኙን ማቅረብ የሚችለው የአጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ በሰጠበት በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው የሚለው አነጋገር የሚፈጥረው ችግር ነው። በአዋጁ አንቀጽ 105(3) በግልጽ እንደተመለከተው አጣሪ ኮሚቴው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሆን በውሳኔ ሓሳብነት ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ የሚቀርብ ነው። ይህም የሚያመለክተው አጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ የሚሰጥበት ቀንና የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ ውሳኔውን የሚሰጥበት ቀን ፈጽሞ የተለያዩ መሆናቸውን ነው። በመሆኑም በሕግ የተመለከተውን የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ ለመቁጠር እንደመነሻ መወሰድ የሚኖርበት የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ ውሳኔ የሰጠበት ቀን ነው እንጂ አጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ የሰጠበት ቀን መሆን አይገባውም። ይህም የቀን አቆጣጠር በሕጉ በግልጽ መደንገግ ይኖርበታል።[175]

---

174 ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔ (tax assessment notice) ቅሬታ በሚያድርበት ጊዜ ቅሬታውን በቀጥታ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለማቅረብ ይችላል። በዚህ ጊዜ ግብር ከፋዩ የይግባኝ አቤቱታውን አሉኝ በሚላቸው ማናቸውም አግባብነትና ተቀባይነት ባላቸው ማስረጃዎች ደግፎ የማቅረብ መብቱ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም። እንደዚሁም ደግም ታክስ ከፋዩ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በሚሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ሲያቀርብ ከአቤቱታው ጋር ማናቸውንም ማስረጃዎች የማቅረብ መብት አለው። ምክንያቱም አጣሪ ኮሚቴው እንደመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለማይቆጠር ማናቸውም ማስረጃዎች በአጣሪ ኮሚቴው ደረጃ መቅረብ አለባቸው ብሎ ማሰብ አይቻልም። በተጨማሪም ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴው የሚያቀርበው እርሱ ራሱ የፈለገ እንደሆነ ነው እንጂ የሚያስገድደው ሕግ የለም። ይህም ማለት አንድ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ቅሬታውን በቀጥታ ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ለማቅረብ ይችላል ማለት ነው። ስለሆነም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ታክስ ከፋዩ አሉኝ የሚላቸው ማስረጃዎች ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር በቀጥታ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው የሚቀርቡ መሆናቸው አነጋጋሪ አይደለም።

175 በሕጉ የተቀመጠው የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ በይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ዘንድ ክርክር ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። ለምሳሌ ያህል በይግባኝ ባይ ማስኮ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርና በመልስ ሰጭ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መካከል በተነሳ ክርክር የአቤቱታ አጣሪው ኮሚቴ ውሳኔ ለይግባኝ ባይ የደረሰው መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም ነበር። ይግባኝ ባይ የይግባኝ አቤቱታውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ያቀረበው ደግሞ ሰኔ 6 ቀን 2001 ዓ.ም ነው። ይህም ሊሆን የቻለው ይግባኝ ባዩ የአጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ እንደደረሰው ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ በማቅረብ ፋንታ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን አዲስ ማመልከቻ በማቅረቡ ይግባኝ ባይ ላቀረበው ማመልከቻ መልስ ሰጭው መልስ ሳይሰጠው የይግባኝ ጊዜው ሊያልፍ በመቻሉ ነው። ይግባኝ ባይ ከላይ በተመለከተው ጊዜ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ሲያቀርብ መልስ ሰጭው ደግሞ በሕጉ የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ይግባኙ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቀረበ። የግብር ይግባኝ ጉባኤውም የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የይግባኝ ባይን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል። *ማስኮ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር V.*

### 3.3.3 የይግባኝ የአቀራረብ ሥርዓትና የማመልከቻው ይዘት

ለግብር ይግባኝ ጉባኤ የሚቀርበው የይግባኝ ማመልካቻ በአካል አልያም ደግሞ በሪኮማንዴ ደብዳቤ በፖስታ ቤት በኩል ሊላክ እንደሚችል በሕጉ ተደንግጓል፡፡ ይግባኙ በቀጥታ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው የሚቀርብ ከሆነ ይግባኙ የቀረበበት ቀን ነው የሚባለው የይግባኝ ማመልከቻው በመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ነው፡፡ የይግባኝ ማመልከቻው በሪኮማንዴ ደብዳቤ በፖስታ ቤት በኩል የሚላክ ሲሆን ይግባኙ የቀረበበት ቀን ሆኖ የሚያዘው የይግባኝ ማመልከቻው በፖስታ ቤት የተመዘገበበት ቀን ነው፡፡[176]

በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጋችን የተደነገጉት የይግባኝ ማመልከቻ አዘገጃጀት መመሪያዎች የታክስ ይግባኝ ማመልከቻን ለማዘጋጀት የሚኖራቸው ጠቀሜታ አጠያያቂ ባይሆንም፣[177] ለግብር ይግባኝ ጉባኤ የሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻ በገቢ ግብር ሕጉ ውስጥ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት አግባብነት ያለው የሕግ ድንጋጌ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 109 ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የይግባኝ ማመልከቻው ግልጽ በሆነ ሁኔታ የይግባኙን ፍሬ ነገርና የይግባኙን ምክንያቶች፣ የግብር ከፋዩን ስም አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የይግባኝ ማመልከቻው ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር በአባሪነት ሊቀርቡ የሚገባቸው አግባብነት ያላቸውን ደጋፊ ሰነዶችና በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን መያዣ የተከፈለባቸውን ደረሰኞች አብሮ መያዝ አለበት፡፡

የይግባኝ ማመልከቻው እነዚህን መስፈርቶች[178] ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ የግብር ይግባኝ ጉባኤው ይግባኝ ባዩ ጉድለቶቹን እንዲያሟላ ይጠይቀዋል፡፡ ይግባኝ ባዩም በአምስት ቀናት ውስጥ ጉድለቶቹን ካላሟላ የቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ወዲያውኑ ውድቅ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡[179] ሆኖም ይህ የአምስት ቀናት ጊዜ ገደብ በጣም አጭር ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አጭር የጊዜ ገደብ ታክስ ከፋዩ ይግባኝ የማቅረብና ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብቱን በአግባቡ እንዳይጠቀምበት የሚያደርግ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ፀሐፊ እምነት ይህ የአምስት ቀናት የጊዜ ገደብ ወደ አሥር ቀናት ወይም አሥራ አምስት ቀናት ከፍ ማለት ይገባዋል፡፡[180]

ይግባኝ ባዩ ያቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ በግብር ይግባኝ ጉባኤው ተቀባይነት አግኝቶ ከተመዘገበና ቁጥርም ከተሰጠው በኋላ የይግባኝ ማመልከቻውና የአባሪዎቹ ግልባጭ በይግባኝ ጉባኤው አማካይነት ለሚመለከተው የታክስ አስገቢ ባለሥልጣን እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ የግብር አስገቢው ባለሥልጣንም  የግብር ይግባኝ ጉባኤው በያዘው የቀጠሮ ቀን መልሱን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የመልሱን ግልባጭ ለይግባኝ ባዩ የመስጠት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡[181]

---

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ* ባለሥልጣን፣ፌደራል ግብር ይግባኝ ጉባዔ፣ መዝገብ ቁጥር ከመ819፣ ያልታተመ፣ ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ.ም ይመልከቱ፡፡

[176] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 108፡፡

[177] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 3/1958፣ በተለይ የወጣ፣ድንጋጌ ቁጥር 52/1958፣ አንቀጽ 327ን ይመልከቱ፡፡

[178] እነዚህ መስፈርቶች የሚለው አገላለጽ የሚወክለው በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 109 ሥር የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ነው፡፡

[179] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 109(2)፡፡

[180] ከዚህ ጸሐፊ ጋር ቃለ-ምልልስ ያደረጉት ምሁራን ዶ/ር ታደሰ ሌንጮና አቶ ዳዊት ተሾመም ይህ የአምስት ቀን ጉዳይ እንደሚያሳስባቸው ለዚህ ጸሐፊ ገልጸውለታል፡፡

[181] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 110፡፡

### 3.3.4. የይግባኝ ክርክሩን ስለመስማት፣ ስለማስረዳት ሸክም እና ውሳኔ ስለመስጠት

በመደበኛው የፍትሐብሔር ይግባኝ ክርክር ጊዜ ፍርድ ቤቱ መልስ ሰጭውን ከመጥራቱ በፊት የቀረበውን ይግባኝ በሚገባ መመርመርና ይግባኝ ባዩንም ማዳመጥ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ከመረመረና ይግባኝ ባዩንም ከአዳመጠ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ምንም ዓይነት እንከን የለበትም ብሎ ካመነ መልስ ሰጭውን መጥራት ሳያስፈልገው መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡[182] ሆኖም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሊፈተሽ ይገባዋል የሚል እምነት ካለው ለመልስ ሰጭው መጥሪያ እንዲደርሰው ተደርጐ የይግባኝ ክርክር መደረግ ይኖርበታል፡፡[183]

የግብር ይግባኝ ጉባኤው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ ይግባኙን የመስማት ኃላፊነት እንዳለበት ወይም ደግሞ ሌላ ሥነ-ሥርዓት መከተል ይችል እንደሆነ በገቢ ግብር ሕጉ አልተመለከተም፡፡ ይሁን እንጂ የግብር ይግባኝ ማመልከቻው በአንቀጽ 109 የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ከተገኘ ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን መጥሪያ እንደሚላክለት ከዚሁ አንቀጽ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት የግብር ይግባኝ ጉባኤው የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ከመቅረቡ በፊት ይግባኝ ባዩን በተናጠል የመስማት ሥልጣንም የለውም፤ ይህንን የማድረግ ኃላፊነትም የለበትም፡፡ በሌላ አነጋገር ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ የግብር ይግባኝ ጉባኤው መልስ ሰጭው ከመጠራቱ በፊት የግብር ይግባኝ ማመልከቻው *"ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም"* ብሎ ብይን የመስጠት ሥልጣን አይኖረውም፡፡

በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሚካሄደው ክርክር ሰነዶችን በመለዋወጥ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ ይልቁንም ተከራካሪ ወገኖች በጉባኤው ፊት ቀርበው ክርክራቸውን በቃል እንዲያሰሙ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተከራካሪ ወገኖች የቃል ክርክር በሚያደርጉበት ጊዜ የጉባኤው አባላት ያልገቧቸውን ነጥቦች ለመጠየቅና ለመረዳት ዕድል ስለሚያገኙ ተከራካሪዎቹ የተለያዩት በምን ጉዳይ ላይ እንደሆነ ለመረዳትና ለውሳኔው አስፈላጊ የሆነውን ጭብጥ ነቅሰው ለማውጣት በእጅጉ ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህም የገቢ ግብር ሕጉ በይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ደረጃ የቃል ክርክር የመስማት ሂደት ሊኖር እንደሚገባው በግልጽ መደንገግ አልያም ደግሞ አግባብነት ያላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ማለት ይገባው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የፌዴራል ግብር ይግባኝ ጉባኤ የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመመልከት ተከራካሪ ወገኖቹ ክርክራቸውን በቃል እንደሚያደርጉ መረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፌደራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚደረገው ክርክር የቃል ክርክር እንደማይታለፍ የጉባኤው አባልና ሰብሳቢ የሆኑ ባለሙያ ለዚህ ጸሐፊ አረጋግጠውለታል፡፡[184]

ከታክስ ይግባኝ ክርክር ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ነጥብ የማስረዳት ሸክም ጉዳይ ነው፡፡[185] የታክስ ክርክር በባህሪይውም ሆነ በውጤቱ ለየት ያለ በመሆኑ በዚህ ክርክር የማስረዳት ሸክም /ኃላፊነት/ በማን ላይ ሊያርፍ ይገባዋል የሚለው ጥያቄ በሁሉም የሕግ

---

[182] የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 176 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 337፡፡

[183] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 338፡፡

[184] አቶ ዳዊት ተሾመም በግብር ይግባኝ ክርክር ጊዜ የቃል ክርክር እንደሚደረግ ለዚህ ጸሀፊ ገልጸውለታል፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 162 የተጠቀሰ፡፡

[185] Bruce L. Hay & Kathryn E. Spier, '*Burden of Proof in Civil Litigation: An Economic Perspective,*' The Journal of Legal Studies, Vol. 26, No. 2 (June 1997), pp. 413-431.

ሥርዓቶች ትኩረት የሚስብ ጉዳይ ነው፡፡[186] የሌሎችን ሀገራት የሕግ ሥርዓት ስንመለከት በመርህ ደረጃ በታክስ ክርክር ወቅት የማስረዳት ሸክም የሚያርፈው በታክስ ከፋዩ ላይ ነው፡፡[187] ለምሳሌ ያህል የካናዳ የታክስ ሕግ በታክስ ከፋዩ ላይ እጅግ ጠንከር ያለ የማስረዳት ሸክም ይጥላል፡፡ በዚህ ረገድ የካናዳ የገቢ ግብር ሕግ ታክስ ከፋዩ ተቃራኒ ማስረጃ አቅርቦ ካላስረዳ በስተቀር፣ ምንም እንኳን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረበትም ማንኛውም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ያስተላለፈው የታክስ ውሳኔ ትክክለኛ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል በማለት ይደነግጋል፡፡[188]

በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም ዓይነት የታክስ ክርክር በሚደረግበት ጊዜ የማስረዳት ሸክም ሙሉ በሙሉ በታክስ ከፋዩ ላይ ማረፍ የለበትም፤ ይልቁንም ይህንን ሸክም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣንም ሊጋራው ይገባል የሚሉ ክርክሮች አሉ፡፡ ይህንን ክርክር የሚደግፉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችም እንዳሉ በመስኩ የተደረጉት የምርምር ሥራዎች ያረጋግጣሉ፡፡[189] ለምሳሌ በአሜሪካ በታክስ ክርክር ወቅት የማስረዳት ኃላፊነት በመርህ ደረጃ የታክስ ከፋዩ ቢሆንም የሀገሪቱ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እ.ኤ.አ በ2006 በሰጠው አንድ ውሳኔ የማስረዳት ሸክሙን ወደ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን አዙሮት ነበር፡፡[190] እንደዚሁም ደግሞ በአውሮፓ መደበኛ ፍርድ ቤቶችና በአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች የይገባኛል ጥያቄ ባነሳው ወገን ላይ የሚያርፈው የማስረዳት ሸክም ከመጠን በላይ የከበደ ወይም ኢፍትሐዊ የሆነ እንደሆነ የማስረዳት ሸክሙ ወደ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ሊዛወር እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡[191]

የኢትዮጵያ የታክስ ሕጎች ዝርዝር የማስረጃ ደንቦችን ባያካትቱም የታክስ ክርክር ሲነሳ የማስረዳት ኃላፊነት ያለበት ታክስ ከፋዩ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ይደነግጋሉ፡፡[192] እነዚህ የታክስ ሕጎች የወሰዱት አቋም በሌሎች ሀገሮች ተግባራዊ የተደረጉ የታክስ ሕጎች ከወሰዱት አቋም ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም[193] የታክስ ሕጎቻችን አቋም ሁልጊዜም ትክክል ነው ብሎ መቀበል ግን ያስቸግራል፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን የማስረዳት ሸክም በታክስ ከፋዩ ላይ የሚያርፍ መሆኑን በመረዳት አንዳንድ የታክስ ውሳኔ የሚያስተላልፉ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች (ኦዲተሮች) በሥልጣናቸው አላግባብ በመገልገልና ለራሳቸው ያልተገባ ጥቅም ከታክስ ከፋዩ ለማግኘት በመሻት ምንም ዓይነት የፍሬ ነገር መሠረት የሌለው የታክስ ውሳኔ በሚያስተላልፉበት ወቅት ታክስ ከፋዩ ይህንን ውሳኔ ለማፍረስ የሚያስችል ምንም ዓይነት ማስረጃ ላይኖረው ይችላል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ወደ አጣሪ ኮሚቴው ወይም ደግሞ ወደ ግብር ይግባኝ ጉባኤ በማቅረብ ፋንታ ከኦዲተሮቹ ጋር መደራደርን ይመርጣል፤ ወይም ደግሞ ሊከፍል የማይገባውን ግብር ለመንግሥት ለመክፈል ይገደዳል፡፡

---

[186] Vern Krishna, '*Reverse Onus of Proof in Tax Litigation,*' The Lawyers Weekly,Vol. 27, No. 42(March 14, 2008), available at <www. Commonlaw.uttowa.com/index-php?option=com_docman>, accessed on July 5, 2013 ገጽ 1፡፡

[187] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 2፡፡

[188] ዝኒ ከማሁ::

[189] David E. Kahen and Elliot Pisem, *The Burden of Persuasion in Tax Litigation*, December 21, 2006, originally published in the Newyork Law Journal, available at <www.robertstandholland.com/Dkahen>, accessed on July 11,2013፣ ገጽ 1፡፡

[190] ዝኒ ከማሁ፡፡

[191] ዝኒ ከማሁ፡፡

[192] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 110(2) እና አንቀጽ 116 ይመልከቱ፡፡

[193] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 186 እና 189 የተጠቀሱትን ሥራዎች ይመልከቱ፡፡

ይህንን ችግር በሚመለከት የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በሥራው አጋጣሚ የተረዳውን አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ እዚህ ላይ ቢገለጽ የችግሩን አሳሳቢነት አጉልቶ ያሳየናል፡፡ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ስሙ እንዲጠቀስ ያልተፈለገ የአንድ የንግድ ድርጅት ሥራ በየሥፍራው የወዳደቁ ቁርጥራጭ ብረታብረቶችን እየለቃቀሙ ከሚሸጡ ግለሰቦች[194] ላይ እነዚህን ብረታብረቶች እየገዛ ለብረታብረት ፋብሪካዎች ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ድርጅት ብረታ ብረቶችን ከእነዚህ ግለሰቦች ሲገዛ ብረቱን ለሚሸጡት ግለሰቦች ገንዘብ መክፈሉ እሙን ቢሆንም ክፍያውን ሲፈጽም ግን ከእነዚህ ግለሰቦች ደረሰኝ ለመቀበል የሚችልበት ዕድል የለውም፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን ወጭ የሚያደርገው በገንዘብ መክፈያ ሰነድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ኦዲተሮች የድርጅቱን የታክስ ኃላፊነት ሲተምሩ ድርጅቱ ብረታብረቶቹን ለመግዛት ያወጣውን ገንዘብ በተቀናሽነት ለመያዝ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ኦዲተሮቹ ድርጅቱ ያወጣውን ገንዘብ በተቀናሽ ለመያዝ ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩት ድርጅቱ ክፍያውን ብረታ ብረት ላቀረቡለት ግለሰቦች የፈጸመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ለማቅረብ ባለመቻሉ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ ሲከሰት የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔው ላይ እንዴት ሊደርስ እንደቻለ አለኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊገደድ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔውን ያስተላለፈው ሕግንና መረጃን መሠረት አድርጎ ከሆነ የውሳኔውን ትክክለኛነት ለማሳየት ማስረጃ ማቅረብ አይቸግረውም፡፡ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የሚወስነውን የታክስ ውሳኔ ሁሉ እውነት ነው ብለን የምንቀበለው ከሆነ በታክስ ካፋዩ ላይም ሆነ በሀገር ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል አያጠራጥርም፡፡

በመሆኑም በመርህ ደረጃ የማስረዳት ሸክም በታክስ ከፋዩ ላይ ማረፍ ቢገባውም በልዩ ሁኔታ ግን በግብር አስገቢው ባለሥልጣንም ላይ የሚያርፍበት ሥርዓት መፈጠር አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር በጥንቃቄና በተጠና ሁኔታ በግብር አስገቢው ባለሥልጣንና በግብር ከፋዩ መካከል የማስረዳት ሸክም ክፍፍል (sharing of burden of proof) መደረግ ይኖርበታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ካለፈው ተሞክሮና ከተሻሩ ሕጎችም ትምህርት ማግኘት ስለሚቻል የማስረዳት ሸክም ክፍፍልን በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ ለመያዝ በ1968 ዓ.ም የደርግ መንግሥት አውጥቶት የነበረውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ግብር አዋጅ[195] መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1) በግልጽ እንደደነገገው ይግባኝ የቀረበበት ገቢ የተወሰነው በግምት ሲሆን ይግባኝ ባዩ ግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት የጠየቀው ግብር አወሳሰን ትክክለኛነት የተቃወመበትን ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ የማስረዳት ሸክም ነበረበት፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር እንደተነገረው ደግሞ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በበኩሉ ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ወይም ሌላ ሰነድ ያልቀረበለት መሆኑን ወይም የቀረበ መዝገብ ወይም ሰነድ ካለም ይኸው ግብር አስገቢው መ/ቤት ከሰጠው መመሪያ ጋር ሲነጻፀር የማያጠግብ ወይም ያልተሟላ ወይም የማይታመን በመሆኑ ተቀባይነት ያለማግኘቱን ወይም በዚህ ዓይነት የተገመተው ገቢ የይግባኝ ባዩ እርሻ ይዞታ ወይም ሁኔታና የኑሮ ደረጃ ታይቶ ሊደረግ የሚገባው ምርመራ ሁሉ ተጠናቅቆ

[194] እነዚህ ግለሰቦች በተለምዶ "ቆራሊዎ" እየተባሉ የሚጠሩት ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ደግሞ በአመዛኙ ቋሚ አድራሻ የሌላቸውና የንግድ ፈቃድም የማያወጡ ተዘዋዋሪ ሰዎች በመሆናቸው ለሚያቀርቧቸው ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች ክፍያ ሲፈጸምላቸው ለከፋዩ ደረሰኝ እንዲሰጡ መጠበቅ የሚቻል አይደለም፡፡

[195] የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ግብር መሰብሰቢያ አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 93 የተጠቀሰ፡፡

በትክክለኛ የሕሊና ፍርድ በማመዛዘን የተወሰነ መሆኑን በሁለተኛ ደረጃ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡[196]

ወደ ታክስ ይግባኝ የመስማት ሂደት ስንመጣ ደግሞ፣ ማንኛውም በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ቅሬታ የተሰማው ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ካቀረበ በኋላ ጉዳዩን የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባዩ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም የመልስ መልስ ሳያቀርብ ቢቀር የግብር ይግባኝ ጉባኤው ይግባኝ ባዩ በሌለበት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡[197] ከዚህም የምንገነዘበው ይግባኝ ባዩ ይግባኙ በሚሰማበት ቀን ያለምንም ምክንያት ቢቀር ይግባኙን የመስማቱ ሥራ ለሌላ ጊዜ ሊዛወር እንደሚችል ነው፡፡ እንዲህ ያለው አካሄድ በኢትዮጵያ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ውስጥ ከተደነገገው ፈጽሞ የተለየ አካሄድ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ[198] አንቀጽ 69(2) በማያሻማ መልኩ እንደተደነገገው ይግባኙ በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባዩ ካልቀረበ ይግባኙ እንደሚዘጋ ነው፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጋችን ያስቀመጠው ጥብቅ መስፈርት በታክስ ሕጎቻችን ተቀባይነት አለማግኘቱንና የግብር ይግባኝ ጉባኤው የላላ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተል ነው፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ተቀባይነት ያለው አቀራረብ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያሉ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ከመደበኛው ፍ/ቤት በባህሪያቸውና በዓላማቸውም ጭምር የተለዩ በመሆናቸው ይግባኝ ባዩን የሚጠቅሙ ላላ ያሉ ሥነ-ሥርዓቶችን እንዲከተሉ መደረጉ አግባብ ነው፡፡[199]

እንዲሁም የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የይግባኝ ባዩ ማመልከቻ ከደረሰው በኋላ በሁለት የቀጠሮ ቀናት ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ለይግባኙ መልስ ሳይሰጥ ቢቀር በሌለበት ውሳኔ እንደሚሰጥ በአንቀጽ 111(4) ሥር ተደንግጓል፡፡ እዚህም ላይ የግብር ሕጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የመረጠውን አካሄድ ያልተከተለ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ይህም ማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኙ በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭው ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ ሲሆን፣[200] ግብር አስገቢው ባለሥልጣን(መልስ ሰጭው) ይግባኙ በሚሰማት ቀን ሳይቀርብ ቢቀር የግብር ይገባኝ ጉባኤው ይግባኙን ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ስለሚሰጥ በመልስ ሰጭው የመሰማት መብት ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ሊኖር እንደማይችል ነው፡፡

---

196 እንደዚህ ጸሐፊ አመለከካት ከዚህ ሕግ ትምህርት መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም በማናቸውም ጊዜ ታክስ ከፋዩ የማስረዳት ሸክም አለበት ማለት፣ ታክስ ከፋዩ ከማይወጣው ማጥ ውስጥ ገብቶ፣ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በማናቸውም ዘዴ የወሰነው የግብር ውሳኔ እንዲፈጸም መፍቀድ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አካሄድ ደግሞ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ተጠያቂነት እንዳይኖርበት ከማድረጉም በላይ ለሙስናም ሰፊ በር የሚከፍት ነው፡፡ ስለዚህ በሁሉም ፍሬነገሮች ላይ የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ብቸኛ ኃላፊነት ነው በማለት ነው በማለት ሕጐቻችን የያዙትን አቋም በተጠና መልኩ ማለዘብ ይኖርብናል፡፡

197 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 111(4)፡፡

198 የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 177 የተጠቀሰ፡፡

199 P.P. Craig፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 የተጠቀሰ፣ገጽ 253፣ ይህ የአስተዳደር ሕግ ምሁር የአስተዳደር ፍርድ ቤቶችን አስፈላጊነት "The reasons for the creation of tribunals have been considered in the historical discussions. A word or two more is warranted at this juncture. It is important to realize that a number of different arguments have been used to justify assigning tasks to tribunals. First, tribunals are often preferred to courts because they have the advantages of speed, cheapness, informality and expertise. …Second,…. ordinary courts might not be sympathetic to the protection of substantive interests contained in the legislation that laid the foundation of welfare state." ሲል ይገልፀዋል፡፡

200 የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 177 የተጠቀሰ፣አንቀጽ 70፡፡

በመጨረሻም የግብር ይግባኝ ጉባኤው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገውን ክርክር ከመረመረ በኋላ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ውሳኔ በገቢ ግብር ሕጉ አንቀጽ 111(1-3) በተደነገገው መሠረት ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣ በጉባኤው ስብሰባ የተገኙ አባላት ዝርዝር፣ የሊቀመንበሩን ስም፣ አግባብነት ኖሯቸው የተጠቀሱትን የሕግ አንቀጾችና የሚገኙበትን ሕግ የሚያብራራ ሆኖ ጉባኤው የደረሰበትን ድምዳሜ፣ ይግባኝ ባይ ሊከፍል የሚገባውን የግብር መጠን፣ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችና በይግባኙ ውስጥ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ትርጉም፣ ይግባኙ በተሰማበት ወቅት በሙሉ በተነሱት አግባብነት ባላቸው በእያንዳንዱ ጭብጦች ላይ የተሰጠውን እልባትና ውሳኔውን በሚመለከት የተሰጠ የሓሳብ ልዩነት ካለ ማካተት አለበት፡፡ በመጨረሻም የተገኙት አባላት ፊርማና የግብር ይግባኝ ጉባኤው ማህተም በውሳኔው ላይ ማረፍ አለባቸው፡፡

ከውሳኔ መስጠት ጋር ተያይዞ መነሳት የሚኖርበት ጥያቄ የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ መስጠት ያለበት በምን ያህል ጊዜ ነው የሚለው ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የግብር ይግባኝ ጉባኤው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን መጨረስ እንዳለበት የሚያስገድድ ድንጋጌ ካለመኖሩም ባሻገር፣ ቢያንስ የታክስ ይግባኝ ክርክር በተቻለ መጠን በፍጥነት ውሳኔ ማግኘት እንዳለበት ማሳሰቢያ የሚሰጥ የሕግ ድንጋጌ እንኳ በሕጎቻችን ውስጥ አልተካተተም፡፡[201] እንደ ግብር ይግባኝ ጉባኤ ያሉ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ከመደበኛው ፍርድ ቤቶች ተለይተው የሚቋቋሙበት ምክንያት በተከራካሪ ወገኖች መካከል ለሚነሱ ክርክሮች በፍጥነት እልባት ይሰጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡[202] ስለዚህም ይህንን ጠቃሚ ግብ እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ወደፊት የታክስ ሕጐቻችንን በሚሻሻሉበት ጊዜ ለዚህ ነጥብ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የግብር ይግባኝ ጉባኤው ልዩ የክርክር መፍቻ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ከመደበኛው ፍርድ ቤት እጅግ ባጠረ ጊዜ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡[203]

### 3.4 በመደበኛ ፍ/ቤቶች የግብር ክፋዮች ቅሬታ አፈታት ሥርዓት

የታክስ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ በአስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንዲስተናገዱ መደረጉ የራሱ ምክንያት ቢኖረውም የታክስ ክርክሮችን በማስተናገድ ረገድ መደበኛ ፍርድ ቤቶችም የሚጫወቱት ሚና ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ አሠራር በአብዛኞቹ ሀገሮች የተለመደ ሲሆን በኢትዮጵያም ውስጥ ቢሆን መደበኛ ፍርድ ቤቶች የተወሰነ ሚና እንደነበራቸው ቀደም ሲል ባቀረብነው ገለጻ ተመልክተናል፡፡ በአሁኑ ጊዜም የታክስ ክርክሮችን በማስተናገድ ረገድ መደበኛ ፍርድ ቤቶቻችን የተወሰነ ሚና እንደሚጫወቱ የታክስ ሕጎቻችን ያሳያሉ፡፡ በዚህ ረገድ ሁሉንም የታክስ ሕጎቻችን ስንመለከት ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው እንገነዘባን፡፡

---

[201] ምንም እንኳን በአተገባበር ደረጃ ሙሉ በሙሉ ተሳክቷል ባይባልም በ1996 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ አሠሪና ሠራተኛ ሕግ በዚህ ረገድ እንደመልካም ምሳሌ መጠቀስ የሚገባው ሕግ ነው፡፡ ይህ ሕግ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚታይ የሥራ ክርክር በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት ብሎ ደንግጓል፡፡

[202] P.P.Craig, ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 የተጠቀሰ፣ ገጽ 253፡፡

[203] በኢትዮጵያ የፍርድ ቤት ክርክር እጅግ አዝጋሚ መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም፡፡ ለአብነትም ያክል ዮሴፍ አእምሮ፣ *'የፍትሐብሔር ክርክሮች ሂደት፡ ፈተናዎችና ተስፋው'*፣ in Yazachew Belew (ed.), The Resolution of Commercial/Business Disputes in Ethiopia: Towards Alternatives to Ajdudication? Ethiopian Business Law Series, Vol.5፣ ከገጽ 1-24 ያለውን ይመልከቱ፣ መንበረፀሐይ ታደሰ፣ *የኢትዮጵያ ሕግና ፍትሕ ገጽታዎች*፣ አዲስ አበባ፣ ኅዳር 1996 ዓ.ም፣ ከገጽ 1-77 ያለውን ይመልከቱ፡፡

የገቢ ግብር አዋጁ[204] አንቀጽ 112(1) የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የይግባኝ ጉባኤው የጽሑፍ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ ስለሕጉ ስህተት ፍርድ ሊጠይቅ ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ውስጥ ሦስት ነጥቦችን በመለየት አጽንኦት ልንሰጣቸው ይገባል፡፡ እነኝህም በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ንዑስ አንቀጽ *"ማንኛውም ተከራካሪ ወገን"* ሲል ግብር አስገቢው ባለሥልጣንም ሆነ ግብር ከፋዩ ቅሬታውን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ እንደሚችል መናገሩ ነው፡፡ ምንም እንኳን በአጣሪ ኮሚቴው ወይም በግብር ይግባኝ ጉባኤ ፊት ቅሬታውን የሚያቀርበው ታክስ ከፋዩ ብቻ ቢሆንም፣ ለምሳሌ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ወይም አጣሪ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው እንደሆነ ለፍ/ቤት ይግባኝ ማለት የሚኖርበት ግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስለሚሆን ግብር ከፋዩ መልስ ሰጭ ሆኖ ይቀርባል ማለት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሁለተኛው ጥያቄ ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የሚችለው በሕግ ስህተት ብቻ ነው ተብሎ ስለተደነገገ የሕግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በሌሎችም ሀገሮች በተደጋጋሚ የሚነሳ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንኳንስ የሕግ ሥርዓታቸው በሚገባ ባላደገባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ቀርቶ የዳበረ የሕግ ሥርዓት ባላቸው ሀገሮችም ዘንድ ቢሆን ለዚህ ጥያቄ የማያሻማ መልስ መስጠት ቀላል ጉዳይ አይደለም፤ ቢሆንም በእነዚህ ሀገሮች ለዚህ አወዛጋቢ ጥያቄ አግባብነት ያለው መልስ ለመስጠት የተለያዩ ጥረቶች እንደተደረጉ በዚህ ረገድ የተደረጉ የምርምር ጽሁፎች ያረጋግጣሉ፡፡[205]

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሁለት ዓይነት ዘዴዎች ሥራ ላይ እንደሚውሉ በመስኩ የተደረጉ የምርምር ሥራዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ዘዴዎች የትንተና ዘዴ (analysis method) እና እንደሁኔታው ሥራ ላይ የሚውል ዘዴ (pragmatic method) የተሰኙ ናቸው፡፡[206] ከትንተና ዘዴ ምልከታ (analysis method) አኳያ አንድ አከራካሪ ነጥብ የፍሬ ነገር ጉዳይ ጭብጥ ነው ሊባል የሚችለው የአንድን ኩነት መኖር ወይም አለመኖር የሚመለከት ሲሆን ነው፤የሕግ ጉዳይ ነው ሊባል የሚችለው ደግሞ ይህ ክስተት በሕግ ረገድ የሚኖረው ፋይዳ ነው፡፡[207] እንደ ሁለተኛው ዘዴ ከሆነ ደግሞ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው ወይስ የሕግ ጉዳይ ነው ብሎ ለመወሰን በሀገሪቱ ያለውን የፖሊሲ አቅጣጫ በሚገባ ማጤን ይገባዋል የሚል ነው፡፡[208] ለምሳሌ ያህል አንድ የውጭ ሀገር ነዋሪ ግለሰብ ከግንቦት ጀምሮ እስከ ጥር ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖርና የኢትዮጵያ ግብር አስገቢ ባለሥልጣን ይህ ግለሰብ በውጭ ሀገር በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር እንዲከፈል ቢወስንበትና አለመግባባት ቢነሳ ይህ የውጭ ሀገር ዜጋ በውጭ ሀገር ገቢ ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለው ጥያቄ በማስረጃ መንጠር የሚገባው ጉዳይ ስለሆነ የፍሬነገር ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ

---

204 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፡፡

205 Taddese Lencho, 'The Ethiopian Tax System: Cutting Through the Labyrinth and Padding the Gaps,' *Journal of Ethiopian Law*, Vol.25, No 1,2011፣ ገጽ 106:: ዶ/ር ታደሰ ሌንጮ በዚህ በምርምር ሥራቸው እንደገለጹት ለምሳሌ በሀገረ እንግሊዝ ይኸው ነጥብ ተደጋግሞ የሚነሳ ጥያቄ ከመሆኑ አንጻር በዚች ሀገር ውስጥ ሰነዶችን ወይም ሕጎችን የመተርጐም ጉዳይ የሕግ ጥያቄ ተደርጐ ሲወሰድ ይህ ሰነድ መቼ ተፈረመ የሚለው ጉዳይ ግን የፍሬ ነገር ጉዳይ እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡

206 K.C.Davis (1958), *Administrative Law Treatise*, St. Paul, Minn. ,West Publishing House Compan, ገጽ 192 ይመልከቱ፡፡

207 Peter Cane, *An Introduction to Administrative Law*, 3rd ed., London Black Stone Press Limited, 1996, ገጽ 64.

208 ዝኒ ከማሁ፡፡

በተቃራኒው ግን ይህ ግለሰብ ለኢትዮጵያ መንግሥት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው የገቢ ግብር ሕጉን ተፈጻሚነት ወሰን በመተንተን በመሆኑ የሕግ ጥያቄ ነው፡፡[209]

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ እስከሚያውቀው ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥም የሕግ ስህተት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ አንድም ሕግ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሰጠው አጥጋቢ መልስ የለም፡፡ ይህ ማለት ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ጥያቄ ተነስቶ አያውቅም ማለት አይደለም፡፡ ይህ ጥያቄ በተለያዩ ጊዜያት ተነስቶ እንደሁኔታው እልባት ሲያገኝ እንደነበር የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ያመለክታሉ፡፡[210] ለምሳሌ ያህል በአቶ ፒዛኖ ኢማኖ እና በክልል አሥራ አራት ዞን አምስት ፋይናንስ ቢሮ መካከል ተነስቶ በነበረ ክርክር የመልስ ሰጭ የአቶ ፒዛኖ ይማኖ ክርክር የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በግምት ግብር መወሰኑ አግባብነት ስለሌለው እና እኔም የሂሳብ መዛግብት ስላሉኝ ውሳኔው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነበር፡፡[211] ይግባኝ ባይ በበኩሉ መልስ ሰጭው የሂሳብ መዛግብትን ያልያዙ በመሆኑ የግብር ውሳኔው በግምት መወሰኑ አግባብነት አለው የሚል ክርክር አንስቶ ነበር፡፡ በመሆኑም የዚህ ክርክር መሠረታዊ ጭብጥ ለመሆኑ አቶ ፒዛኖ የሂሳብ መዝገብ ይዘው ነበር ወይስ አልነበረም የሚለው ነጥብ በመሆኑ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩ የፍሬነገር ጉዳይ ነው በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጉታል፡፡ ይህም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ትክክለኛ ውሳኔ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ነጥብ በማስረጃ የሚነጥር የፍሬነገር ጉዳይ እንጂ ሕግ በመተንተን መልስ ሊሰጠው የሚችል ጭብጥ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተያዘውን ጉዳይ አስመልክቶ በ2002 ዓ.ም የሰጠውን ገዥ ውሳኔ ማንሳቱ አግባብነት አለው፡፡ በዚህ ክርክር አመልካች የነበረው አቶ አብደላ ሁሴን ከለር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲሆን መልስ ሰጭው ደግሞ የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነበር፡፡[212] መልስ ሰጭው መ/ቤት ለአመልካቹ በገቢ ግብርና በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የግብር ማስታወቂያ ሲሰጠው አመልካቹ በበኩሉ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ለማቅረብ በመፈለጉ በሕጉ መሠረት የሚያስይዘውን ገንዘብ ለሁለቱም የታክስ ዓይነቶች ሁለት የተለያዩ ሲፒኦዎችን አሠርቶ ለባለሥልጣኑ አቅርቧል፡፡ ይህ የመያዣ ሲፒኦ የቀረበው ግን አመልካቹ የግብር ውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ30ኛው ቀን ዓርብ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ነበር፡፡ ባለሥልጣኑም የገቢ ግብርን አስመልክቶ የቀረበውን ሲፒኦ ተቀብሎ ለአመልካች ደረሰኝ ቢሰጥም ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ የቀረበውን ሲፒኦ ተቀብሎ የኮምፒዩተር ብልሽት አጋጥሞናል በማለት ለአመልካቹ ደረሰኝ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡ ቀጣዩቹ ቀናት (ማለትም ሰኔ 9 እና ሰኔ 10) ቅዳሜና እሁድ ስለነበሩ ተጠሪው ለአመልካቹ ደረሰኙን የሰጠው ሰኞ ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ነበር፡፡

ከዚህ በመቀጠል አመልካቹ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ቢያቀርብም የግብር ይግባኝ ጉባኤው ግን በሕጉ የተመለከተው የ30 ቀን ገደብ አልፏል በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው

---

209 የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ ከአንቀጽ 3-5 ያሉትን ድንጋጌዎችይመልከቱ፡፡

210 Taddese Lencho፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 205 የተጠቀሰ፣ ገጽ 107፡፡

211 Melkamu Belachew፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 17 የተጠቀሰ፣ ገጽ 60::

212 አቶ አብደላ ሁሴን ከለር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር V. የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን፣ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 48621፣የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች፣ ቅጽ 10፣ ከገጽ 365-367፡፡

ቀረ፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ አመልካቹ ለይግባኝ ምክንያት ያደረገው በሕጉ የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ሊያልፍብኝ የቻለው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ደረሰኙን በወቅቱ ባለመቁረጡ ነው እንጂ በእኔ ጥፋት ባለመሆኑ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ያቀረብኩት ይግባኝ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባዋል በማለት ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ክርክሩ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የሕግ ክርክር ባለመሆኑ በፍ/ቤት ሊታይ አይገባውም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካቹ ሁለተኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ ምክንያት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ስለዚህ አመልካቹ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አቅርቧል፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ የሚከተለውን ሀተታ በማስፈር ሽሮታል፡-

> *… ሕግ አውጭው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሰዎች የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሠላሳ ቀን ውስጥ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 50% ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን በማስያዝ ይግባኝ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 285/94*[213] *አንቀጽ 43(1) ሲደነግግ ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማስገደድ እንጂ ገንዘቡ ገቢ ሆኖ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን ደረሰኝ ሳይሰጥ ቢቆይ በመ/ቤቱ የአሠራር ድክመትና ችግር ምክንያት ግብር ከፋይ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንዲጣበብበት በማሰብ አይደለም፡፡ … በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት በኩል ያሉ የአሠራር ችግሮችና ጉድለቶች መሠረታዊ የሆነውን የአመልካችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በማያጣብብ ሁኔታ በመተርጐም፣ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ የሕጉን ድንጋጌ አተረጓጐምና ተፈጻሚነት የሚመለከት እንጂ የፍሬ ጉዳይ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍ/ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎቶች ጉዳዩ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ … የሰጠውን የተዛባ ውሳኔ ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡*

ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው የግብር ይግባኝ ጉባኤው፣ የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደፈጸሙ ነው፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ያለው አቤቱታ አግባብነት ያለውን ሕግ የመተርጎም ዘዴ በመከተል የሕግ አውጭውንም ሐሳብ መመርመርና ማረጋገጥ የሚጠይቅ ጉዳይ በመሆኑ የፍሬነገር ጉዳይ ነው ተብሎ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሰበር ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎምን የተከተለና የታክስ ከፋዩንም የመሰማት መብት በጥሩ ሁኔታ ያገናዘበ ውሳኔ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊነሳ የሚገባው ነጥብ የገቢ ግብር አዋጁ በአንቀጽ 112(1) *ሥር ይግባኙ የሚቀርበው ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ነው* ሲል ምን ማለቱ ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሀገራችን የፌዴራል ሥርዓት የምትከተል ሀገር እንደመሆኗ መጠን ፍ/ቤቶቻችንም የተዋቀሩት በክልልና በፌዴራል ደረጃ ነው፡፡[214] በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

---

[213] ይህ አዋጅ ከላይ በግርጌ ማስተወሻ 45 የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[214] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 50(2)፡፡ በተጨማሪም ከአንቀጽ 78-82 ያሉትን ሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎች ይመልከቱ፡፡

ተቋቁመዋል፡፡[215] ከእነዚህ የፍርድ ቤቶች እርከን ውስጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስሙም እንደሚጠቁመው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ከግብር ይግባኝ ጉባኤው የሚቀርብ ይግባኝ ተቀብሎ ለመመልከት እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡[216] በመሆኑም በግብር ይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት ወገን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መደበኛው ፍ/ቤት የሚሄደው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቀርብ ነው፡፡ ይግባኙ የሚቀርብለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተቀብሎ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጋችን በሚያዘው መሠረት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር ከመረመረ በኋላ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የወሰነው ውሳኔ ምንም እንከን የለበትም ብሎ ካመነ መልስ ሰጭውንም መጥራት ሳያስፈልገው መዝገቡን ሊዘጋው ይችላል፡፡[217]

በሌላ በኩል ግን ይህ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግብር ይግባኝ ጉባኤው በሰጠው ፍርድ የሕግ ስህተት መፈጸሙን የሚያመላክት ነገር አለው ብሎ ካመነ ይግባኙ ያስቀርባል ይልና ለመልስ ሰጭው መጥሪያ እንዲደርሰው በማድረግ ሁለቱን ወገኖች ከአከራከራቸው[218] በኋላ የግብር ይግባኝ ጉባኤውን ውሳኔ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡[219] ይህንን ስንል ግን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለቀረበለት ጉዳይ የመጨረሻ እልባት ( final disposition) ይሰጠዋል ማለታችን አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ ፍ/ቤት የግብር ይግባኝ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ከሆነ የተፈፀመውን ስህተት ለይቶ በማውጣትና ስህተቱን በማቃናት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ይመልስለታል፡፡

ሆኖም ግን እዚህ ላይ ሁለት መሠረታዊ ትችት አዘል አስተያየቶች ይሰነዘራሉ፡፡ የመጀመሪያው አስተያየት ከፍተኛው ፍ/ቤት የሚመለከተው የሕግ ስህተትን ብቻ ነው ተብሎ በሕግ መደንገጉ የታክስ ከፋዮችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በእጅጉ የሚያጣብብ በመሆኑ በግብር ይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ ላይ ማንኛውም ዓይነት ቅሬታ (በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ) ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ለከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲያቀርብ ቢፈቀድለት መልካም ነው የሚል ነው፡፡[220] ሁለተኛው አስተያየት ደግሞ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ከመረመረ በኋላ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ከተረዳ ጉዳዩን ወደ ግብር ይግባኝ ጉባኤው እንዲመለስ ከማስገደድ ይልቅ ጉዳዩን ራሱ እንዲመለከተው ወይም ደግሞ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው እንዲመልስ የማዘዙ ሥልጣን ለፍ/ቤቱ ቢተውለት ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል ነው፡፡[221] ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ የግብር ይግባኝ ጉባኤው

---

[215] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 78(2) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ሕገ-መንግሥት የተቋቋመ መሆኑን ይደነግግና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሚያቋቋም አረጋግጧል፡፡ በዚህም መሠረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በ1988 ዓ.ም ሲታወጅ የኋለኞቹ ሁለት ፍርድ ቤቶች ተቋቁመዋል፤ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ 2ኛ ዓመት፣ቁጥር 13 ይመልከቱ፡፡

[216] የግብር ይግባኝ ጉባኤው ደረጃና ሥልጣን ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጋር እኩል ነው እንደማለት ነው፡፡

[217] የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 177 የተጠቀሰ፣ በአንቀጽ 337 የተደነገገውን ይመልከቱ፡፡

[218] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 338፡፡

[219] ዝኒ ከማሁ፡፡

[220] ይህንን አቋም የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በጣም የሚደግፈው ሲሆን፣ሌሎች ግለሰቦችም ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው ጸሀፊው በተለያዩ ጊዜያት የታክስ ሕግን ሲያስተምር ለመገንዘብ ችሏል፡፡

[221] ዝኒ ከማሁ፡፡

በሕግ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው ብሎ በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ይኸው ውሳኔ ለጉዳዩ መቋጫ ሊያበጅለት ይችላልና ነው፡፡[222]

አሁን በሥራ ላይ ያለው የፍርድ ቤቶቻችን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደሚደነግገው አንድ ተከራካሪ ወገን ያለው የይግባኝ መብት ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም በገቢ ግብር አዋጁ በአንቀጽ 112(3) በግልጽ እንተደነገገው የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት[223] በሕግ ረገድ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚቀጥለው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ይችላል፡፡ ይህም የሚያሳየው በታክስ ክርክር ጊዜ ሁለት ጊዜ ይግባኝ ማለት የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሊያይ የሚችለው የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚያየውን የሕግ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ይህ ሕግ በ1988 ዓ.ም የወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ይግባኝን አስመልክቶ የወሰደውን አቋም ያልተከተለ መሆኑን ነው፡፡

እንዲሁም ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሕግ ጉዳይን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት እንደሆነ አቤቱታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የማቅረብ መብት አለው፡፡ ተካራካሪ ወገኖች በዚህ መብት ሊሰሩበት የሚችሉት ይህ መብት በታክስ ሕጐቻችን ውስጥ ስለተደነገገ ሳይሆን በሕገ-መንግሥቱና በፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የተደነገገ መብት ስለሆነ ነው፡፡ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እንደተነገረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማንኛውም የበታች ፍ/ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለበት ጉዳዩን ተቀብሎ የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ 10 ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት *መሠረታዊ የሕግ ስህተት* ያለባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች የማየት ሥልጣን እንዳለው ዘርዘር ባለ መልኩ ደንግጓል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተራ የሕግ ስህተቶች ያሉባቸውን ጉዳዮች ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡[224] ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን አስቸጋሪ ሆኖ የዘለቀው ጉዳይ አንድን የሕግ ስህተት ተራ ወይም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል መመሪያ አለመኖሩ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

---

[222] ለምሳሌ ያህል አንድ ስጦታ የተደረገለት ሰው ባገኘው የስጦታ ገንዘብ ላይ የገቢ ግብር መክፈል አለበት ወይስ የለበትም የሚል ጭብጥ ለከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ቀረበለት እንበል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ከስጦታ የሚገኝ ገቢ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ሥር ከተመለከቱት የገቢ ግብር ማስከፈያ ሠንጠረዦች ሥር ያልተካተተ በመሆኑ ስጦታ ተቀባዩ የገቢ ግብር መክፈል አይኖርበትም ብሎ ቢወስን ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ሰጥቶታል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ተመልሶ የሚላክበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይገባውም፡፡

[223] ከግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ተቀብሎ የሚሰማውን ፍርድ ቤት (በፌደራል ደረጃ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት) የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ነው የምንልበት ምክንያት ይግባኝ ጉባኤው እንደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚቆጠር አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ለፌ/ከ/ፍ/ቤት የሚቀርበው ይግባኝ መደበኛው ፍርድ ቤትን በተመለከተ የመጀመሪያ ይግባኝ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ወደ ፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚባል ከሆነ ሁለተኛ ይግባኝ እንደሆነ የሚያነጋግር አይደለም፡፡

[224] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 80(3(ሀ) እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 216 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 10፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎት ማንኛውንም የሕግ ስህተት አለበት የተባለውን ውሳኔ ተቀብሎ ለማየት ተገድዷል፡፡[225]

ምንጊዜም ቢሆን ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርበው አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እናም ለሰበር ሰሚው ችሎት የሚቀርበው የሰበር አቤቱታ ይዘት አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች የተገለፁትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡[226] በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ተከራካሪ ወገን አቤቱታውን ለሰበር ሰሚው ችሎት ማቅረብ የሚገባው ውሳኔው ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ ነው፡፡[227] በዚህ ዓይነት የቀረበው የሰበር ማመልከቻ ለአምስት ዳኞች ከመቅረቡ በፊት ሦስት ዳኞች ለሚሰየሙበት የማጣሪያ ችሎት መቅረብ ይኖርበታል፡፡[228] እነዚህ ሦስት ዳኞች ጉዳዩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ካሉ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ለሚሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት ይቀርብና ክርክር ይደረግበታል፡፡[229]

ሰበር ሰሚው ችሎትም የተከራካሪ ወገኖቹን ክርክር ከመረመረ በኋላ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የሰበር ሰሚው ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት አለው፡፡[230] በመሆኑም በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራልም ሆነ የክልል የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠውን የሕግ ትርጉም መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ጉባኤዎች መደበኛ ፍ/ቤቶች ባይሆኑም የታክስ ሕግን በተመለከተ ግን እንደፍርድ ቤት ሆነው ሕግን የሚተረጉሙና ውሳኔ የሚሰጡ አስተዳደራዊ ፍ/ቤቶች በመሆናቸው የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ እነሱንም ይመለከታቸዋል፡፡[231]

---

[225] ይህን ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን የምርምር ሥራዎች ይመልከቱ፡- ዮሐንስ ኀሩይ፣ *'ስለሰበር ሥልጣንና ሥርዓቱ ጥቂት ማስታዎሻዎች'*፣ የኢትዮጵያ ጠበቆች የህግ መጽሄት፣ቮልዩም 3፣ ቀጥር 1, መጋቢት 2001፣ ከገጽ. 131-148፣ Muradu Abdo, '*Review of Decisions of State Courts over State Matters by the Federal Supreme Court*,' *Mizan Law Review*, Vol. 1, No 1, June 2007, pp. 60-74. መሀሪ ረዳኢ፣ *'የፌደራል የሰበርና የሰበር ሰበር የሥልጣን ምንጭ ገልጠን ብናየው! (በሰበር መ.ቁ 26996 እና 31601 መነሻነት የቀረበ ትችት)'*፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 24 ፣ቁጥር 2, ታህሳስ 2003፣ ዓ.ም፣ ከገጽ. 201-213፡፡

[226] በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጋችን ውስጥ ሰበርን በተመለከተ የሚደነግጉ አናቅጽ ባይኖሩም፣ ለሰበር ሰሚው ችሎት የሚቀርበው አቤቱታ በቅርፅና በይዘት ከይግባኝ ማመልከቻ የተለየ አይደለም፡፡ በመሆኑም በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጋችን ውስጥ ይግባኝን በሚመለከት የተደነገጉት አንቀጾች የሰበር አቤቱታ ለማዘጋጀትም ያገለግላሉ፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎት ክርክሩን የሚመራውም ሆነ ውሳኔ የሚያስተላልፈው የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጉን ተከትሎ እንደሆነ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡

[227] የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 215 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 22(1)፡፡

[228] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ

[229] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 21(2(ሐ)፡፡

[230] የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 454/1997፣11ኛ ዓመት፣ ቁጥር 42፣ አንቀጽ 2(1)፡፡

[231] የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አሳትሞ ያሰራጫል በማለት የአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ይደነግጋል፡፡

በመጨረሻም መነሳት ያለበት ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ከመረመረ በኋላ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ውሳኔ ቢሰጥ ለጉዳዩ እራሱ የመጨረሻ እልባት ይሰጥበታል? ወይስ ወደታች ፍ/ቤቶች መልሶ ይልከዋል? ወይስ በቀጥታ ወደሚመለከተው ግብር ይግባኝ ጉባኤ ይመልሰዋል? የሚለው ጥያቄ ነው። የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ እስከሚያውቀው ድረስ የታክስ ሕጎቻችንን አልያም ሌሎች ሕጎቻንን በመመርመር ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት አንችልም። ሆኖም ግን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአንድ የታክስ ክርክር ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሳኔ ይህንን ነጥብ በሚመለከት የሰበር ሰሚው ችሎት አቋም ምን እንደሆነ ሊያስገነዝበን ይችላል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሰበር ሰሚው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት ውሳኔያቸውን ውድቅ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን በቀጥታ ለፌዴራል ግብር ይግባኝ ጉባኤ መልሶታል።[232] ሰበር ሰሚው ችሎት የወሰደው አቋም ትክክለኛ አቋም ነው። ምክንያቱም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ተብሎ ውሳኔያቸው ውድቅ ከተደረገ በኋላ ጉዳዩ ወደእነሱ ተመልሶ የሚሄድበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባውምና ነው። ይሁን እንጂ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወሰደውን አቋም በማያሻማ መልኩ የሚደነግግ ሕግ ባለመኖሩ ወደፊት የታክስ ሕጎቻችንም ሆነ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የሥነ-ሥርዓት ሕጎች በምናሻሽልበት ጊዜ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ልንሰጠው እንደሚገባ የጸሀፊው እምነት ነው።

### 3.5. በአፈጻፀም ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች እንዴት ይስተናገዳሉ?

በሀገራችን የተደረገው የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ካመጣቸው መሠረታዊ ለውጦች መካከል አንዱና ዋነኛው የታክስ ውሳኔ አፈጻፀም ጉዳይን የሚመለከተው ነው። ስለሆነም አዳዲሶቹ የታክስ ሕጎች ከወጡ ወዲህ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔዎችን ለማስፈጸም ፍርድ ቤት መሄድ አያስፈልገውም።[233] ምክንያቱም እነዚህ ሕጎች በማያሻማ ሁኔታ እንደደነገጉት የታክስ አስገቢው ባለስልጣን የማንኛውንም የታክስ ውሳኔ የተላለፈበትንና ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ንብረት በማገድና በመሸጥ ከሽያጩ የሚገኘውን ገንዘብ ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገውን ታክስ ለመሸፈን ያውለዋል።[234]

ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትን የሀገራችን የታክስ ሕጎች ስንመረምራቸው የታክስ ውሳኔ በሚፈጸምበት ጊዜ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዩ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ የሚደነግጉት ነገር የለም። ነገር ግን የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በአፈጻጸም ጊዜ በታክስ ከፋዩ ላይ በደል ቢያደርስበት በደል የደረሰበት ታክስ ከፋይ የደረሰበትን በደል አስመልክቶ ቅሬታ የማቅረብና መፍትሔ የማግኘት የማይገሰስ መብት አለው። ይህንንም ለማለት የሚቻለው በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገውን አቤቱታ የማቅረብና የመሰማት መሠረታዊ መብት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።[235] በመሆኑም በታክስ ውሳኔ አፈጻጸም ወቅት ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴው ወይም ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር ሊኖር አይገባም ብሎ መከራከር ይቻላል። በአንፃሩም፣ በአፈፃጸም ጊዜ የሚነሱ አለመግባባቶች የግድ በግብር ይግባኝ ጉባኤ በኩል ማለፍ አለባቸው የሚል የሕግ ድንጋጌ

---

[232] ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 213 የተጠቀሰውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ይመልከቱ።

[233] የገቢ ግብር አዋጅ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 28 የተጠቀሰ፣ ከአንቀጽ 77-83 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመልከቱ።

[234] ዝኒ ከማሁ።

[235] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ ከላይ በማታወሻ ቁጥር 26 የተጠቀሰ፣ አንቀጽ 37።

በታክስ ሕጎቻችን ውስጥ ስለሌለ በአፈጻጸም ጊዜ ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ሥልጣን ላለው መደበኛ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደው ነገር ሊኖር አይችልም ብሎ መከራከር ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳም ሌላ ጥያቄ አለ፡፡ የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን በወሰደው የአፈጻጸም እርምጃ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው አቅርቦ የግብር ይግባኝ ጉባኤውም ቅሬታውን ቢቀበለውና፣ ከዚያም በመቀጠል ቅሬታ ያደረበት ታክስ ከፋይ የግብር ይግባኝ ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የአፈጻጸም ሂደቱ ታግዶ እንዲቆይ የሚል አቤቱታ ቢያቀርብ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የጥያቄውን አግባብነት ገምግሞ በአፈጻጸሙ ላይ የእግድ ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል ወይ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ በመሠረቱ በአፈጻጸም ሂደት የሚነሱ ክርክሮችን (አለመግባባቶችን) ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችለው ግልጽ ሥልጣን ያልተሰጠው የግብር ይግባኝ ጉባኤ አፈጻጸሙ እንዳይቀጥል የእግድ ትእዛዝ ለመስጠት የሚያስችለው ሥልጣን በሕግ እንዳልተሰጠው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመሆኑም አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች በአፈጻጸም ላይ የሚነሱ ክርክሮች እልባት እስኪያገኙ ድረስ አፈጻጸሙ እንዳይቀጥል የእግድ ትዕዛዝ ሊያስተላልፉ ይችላሉ ብሎ መጠበቅ የሚቻል አይመስልም፡፡[236]

በመሆኑም በታክስ ውሳኔ አፈጻጸም ሂደት ቅሬታ የሚኖረው ታክስ ከፋይ ሁለንተናዊ መፍትሔ ማግኘት የሚችለው ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ቢወስደው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ታክስ ከፋዩ ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤትም ሲወስደው ከፍ/ቤቱ በኩል ፈተና እንደሚገጥመው መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የታክስ ውሳኔ የማስፈጸም ተግባር ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች የወጣ በመሆኑ እንዲህ ያለው ጉዳይ ለመደበኛው ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል አይደለም የሚል አቋም ከፍ/ቤቶቹ በኩል ሊነሳ ስለሚችል ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በታክስ ውሳኔ አፈጻጸም ጊዜ በደል የሚደርስበት ታክስ ከፋይ በደሉን የሚያቀርብበትና መፍትሔ የሚያገኝበት ግልጽ ሥርዓት ያልተበጀለት መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ዋና ችግር ዘላቂ መፍትሔ የሚሆነው የታክስ ሕጎቻችንን በማሻሻል እንዲህ ዓይነቱ ችግር የሚፈታበትን ዘዴ በማያሻማ አኳኋን መደንገግ ነው፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በዝርዝር እንደተገለጸው የታክስ ከፋዮች ቅሬታዎች የሚስተናገዱባቸው የሕግና ተቋማዊ ማዕቀፍ ሥራ ላይ መዋላቸው ባይካድም የታክስ ከፋዮች ቅሬታ የሚስናገዱበት ሥርዓት በርካታ ችግሮች ያሉበት ስለሆነ ለእነዚህ ችግሮች ተገቢውን መፍትሄ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በታክስ ከፋዮች መካከል ሊነሱ የሚችሉት አለመግባባቶች በጣም ዘርፈ-ብዙ ቢሆኑም፣ ለአጣሪ ኮሚቴው የተሰጠው ሥልጣን በታክስ ውሳኔ ላይ (tax assessment) የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መመርመርና የውሳኔ ሓሳብ መስጠት ብቻ ነው፡፡ የአጣሪ ኮሚቴው ሥልጣን በጣም ጠባብ በመሆኑ ለኮሚቴው የሚሰጠው ሥልጣን በታክስ አስገቢው ባለሥልጣንና በግብር ከፋዩ መካከል ሊነሱ የሚችሉትን ክርክሮች ሁሉ ለማስተናገድ የሚያስችለው መሆን ይገባዋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለአጣሪ ኮሚቴው ማቅረብ

---

[236] ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ በሚመለከት አቶ ምስጋናው ጋሻው የሰጠውን ትንታኔ ይመልከቱ፤ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰ፣ ከገጽ 49-51፡፡

የሚኖርበት የታክስ ውሳኔው በደረሰው በአሥር ቀናት ውስጥ ነው መባሉ አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ይህ ጊዜ ከመጠን በላይ አጭር ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢ ጥናት ተደርጎበት ይህ የአሥር ቀን የጊዜ ገደብ ወደ ሃያ ወይም ደግሞ ወደ ሠላሳ ቀናት ከፍ ቢደረግ የታክስ ከፋዮችን የመሰማት መብት ለማረጋገጥ በእጅጉ ይረዳል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው ለማቅረብ በቅድሚያ የሚከፈለው አከራካሪው የታክስ መጠን 50% ክፍያ በጥሬው ገንዘብ ብቻ እንዲከፈል መደረጉ የታክስ ከፋዮችን ይግባኝ የማለት መብት የሚያጣብብ ስለሚሆን የታክስ ከፋዮች ይህንን ግዴታ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችሏቸው ሌሎች አማራጮችም (ለምሳሌ እንደ ፋይናሻል ጋራንቲ ቦንድ) ቢታዩ የታክስ ሥርዓቱን ፍትሐዊነትና የግብር ይግባኝ ጉባኤውን ብሎም የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ለማረጋገጥ በጎ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡

የግብር ይግባኝ ጉባኤው አባላት በምን መስፈርት እንደሚመረጡ እና ከየትኛው መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት እንደሚመረጡ የሚደነግግ መመሪያ ማውጣት እንደሚገባ በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፣ ይህ ኃላፊነት የተጣለበት የፍትሕ ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ እስካሁን ድረስ አለማውጣቱ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ይህ መ/ቤት በውክልና የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ግደታውን በማክበር ይህንን መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የመመሪያው መውጣት የግብር ይግባኝ ጉባኤው አባላት የሚመረጡበትን መስፈርቶችና ስብጥር ለመወሰን ስለሚረዳ የግብር ይግባኝ ጉባኤውንም አሠራር እንደሚያሻሽለው ይገመታል፡፡

አሁን ባለው የግብር ይግባኝ ጉባኤው አሠራር የጉባኤው አባላት የሚመለመሉት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ከፍትሕ ሚኒስቴር ሠራተኞች መካከል ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የተወሰኑት የጉባኤው አባላት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሠራተኞች መካከል መመረጣቸው የጉባኤውን ነፃነትና ገለልተኝነት አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም በታክስ ከፋዮች ላይ ቅሬታ የሚያሳድሩት አንድም በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚወሰኑ የታክስ ውሳኔዎች አልያም ደግሞ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣቸው መመሪያዎች ወይም የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች በመሆናቸው እነዚህ የመንግሥት ተቋማት የታክስ ከፋዮችን ቅሬታዎች ለመስማት ተወካዮቻቸውን እንዲልኩ ከተፈቀደላቸው በእራሳቸው ጉዳይ እራሳቸው ዳኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አሠራር ደግሞ የታክስ ከፋዮችን ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት በእጅጉ የሚፃረር ስለሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባውም፡፡ ስለሆነም የጉባኤውን ነፃነትና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚወከሉ ግለሰቦች የጉባኤው አባላት መሆን አይገባቸውም፡፡ ይልቁንም በእነዚህ ግለሰቦች ምትክ በታክስ ዕውቀታቸውና ልምዳቸው የታወቁ ግለሰቦች ከንግዱ ማኅበረሰብና ከሕግ ባለሙያዎች በግብር ይግባኝ ጉባኤው ውስጥ በአባልነት ቢካተቱ የጉባኤውን ነፃነትና ገለልተኝነት ለማረጋገጥና የታክስ ከፋዮችንም ፍትሕ የማግኘት መብት በተግባር ለመተርጎም አመቺ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ማንኛውም ግብር ከፋይ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብር ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ሲያቀርብ የይግባኝ ማመልከቻው በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት እንደሚኖርበት እሙን ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ሕጉ የሚጠይቃቸውን መስኪያዎች የይግባኝ ማመልከቻው ሳያሟላ ሲቀር ይግባኝ ባዩ ማመልከቻውን አሻሽሎ ወይም መያያዝ ያለባቸውን ሰነዶች አያይዞ እንዲቀርብ የሚፈቀድለት መሆኑ በሕጉ መደንገጉ መልካም ሆኖ ሳለ፣ ማመልከቻውን አሻሽሎ ወይም መያያዝ የሚገባቸውን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ የሚችለው በአምስት ቀናት ብቻ ነው ተብሎ በአዋጅ መደንገጉ አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ይህ የአምስት ቀን ገደብ

አጅግ አጭር ከመሆኑም በተጨማሪ እንዲህ ያለው ጉዳይ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ ስለሆነ በውክልና ሕግ የማውጣት ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚወሰን ጉዳይ እንጂ በሕግ አውጭው የሚወሰን ሊሆን አይገባውም። ስለዚህ ወደፊት የታክስ ሕጎቻችን በሚሻሻሉበት ጊዜ ለእነዚህ ነጥቦች ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የታክስ ሕጎቻችን በማናቸውም ጉዳይ ላይ የማስረዳት ኃላፊነት ያለበት ግብር ከፋዩ እንደሆነ ደንግገዋል። ይሁን እንጂ እንዲህ ያለው አካሄድ በታክስ ከፋዮች ላይ የማይገባ ጫና የሚፈጥርና የታክስ ከፋዮችንም አቤቱታ የማቅረብና የመስማት መብት በእጅጉ የሚጎዳ ነው። በመሆኑም የታክስ ሕጎቻችንን በማሻሻል የማስረዳት ሸክም እጅግ በተጠና መልኩ በታክስ ከፋዮችና በግብር አስገቢው ባለሥልጣን መካከል የሚከፋፈልበትን ዘዴ መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

በግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ጉዳዩን ወደመደበኛው ፍ/ቤት መውሰድ የሚችለው በሕግ ጉዳዮች ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ጉዳይ የሕግ ጉዳይ ይሁን ወይም የፍሬነገር ጉዳይ ለመለየት የሚያስችል ምንም ዓይነት መመሪያ ባለመውጣቱ ታክስ ከፋዮች ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው መፍትሔ ለማግኘት ችግር እየገጠማቸው ነው። ምክንያቱም አንድ ጉዳይ የሕግ ጉዳይ ነው ወይስ የፍሬነገር ጉዳይ ነው የሚለው ነጥብ በፍርድ ቤቱ ነፃ ፈቃድ (discretionary power) የሚወሰን ስለሆነ ነው:: በመሆኑም በታክስ ከፋዮች ላይ በዚህ ረገድ የሚደርሰውን ችግር ለመቀነስ አንድ ጉዳይ የፍሬነገር ጉዳይ ወይም የሕግ ጉዳይ መሆኑን ለመወሰን የሚያስችሉ መመሪያዎችን በሕግ መደንገግ ወይም ደግሞ ይህንን ማድረግ የማይቻል ከሆነ መደበኛው ፍርድ ቤት በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሚነሱ የግብር ይግባኝ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። ሁለተኛውን አማራጭ መከተል የሚያስፈልግ ከሆነ በፍርድ ቤቶቻችን ውስጥ የታክስ ችሎቶች ማቋቋምና በታክስ ላይ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ዳኞች መመደብ ተገቢ ይሆናል።

በመጨረሻም በታክስ ውሳኔ አፈጻጸም ጊዜ በታክስ ከፋዮች ላይ የሚደርሱ በደሎች እንደምን ሊስተናገዱ እንደሚችሉ የሀገራችን የታክስ ሕጎች የሚደነግጉት ነገር የለም። ስለሆነም የታክስ ሕጎቻችንን በማሻሻል የታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የታክስ ውሳኔዎችን በሚፈፅምበት ወቅት በደል የደረሰበት ታክስ ከፋይ ቅሬታ የሚያሰማበትንና መፍትሔ የሚያገኝበትን ግልጽ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ■